በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥር ፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል እና የሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ i

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ታሪካዊ ሂደት 1

የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ስልጣንና ተግባር 2

የባለሥልጣኑ ራዕይ 2

የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ተልዕኮ 2

የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ዓላማ 2

የባለሥልጣኑ ስልጣንና ተግባር 3

የባለሥልጣን መ/ቤቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል መዋቅራዊ አደረጃጀት 5

የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰው ሃይል 6

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ 6

መደበኛ በጀት 6

የቁጥጥር ሥራ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION) 7

የኮንስትራሽን የኩባንያዎች እና ባለሙያዎች የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION) 8

የኦዲቱ ዓላማ 9

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ 9

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች 9

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት 10

ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 10

ክፍል ሁለት 12

የኦዲት ግኝቶች 12

I. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቋረጡ የፌደራል መንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምዝገባና ቁጥጥር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤ 12

የተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ 12

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ከብልሽት መጠበቃቸውን በተመለከተ 17

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና አፈፃፀም በተመለከተ 19

ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ 27

የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርጉ ባለሙያዎች የተመደቡ መሆኑን በተመለከተ 35

ለተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ቁጥጥር እና ለሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ ለማሻሻል ጥናቶች መካሄዳቸውን በተመለከተ 36

II. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ህጎች መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ 39

የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ በተመለከተ 39

በኮንስትራክሽን ስራዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎችን መረጃ አያያዝንና ክትትል በተመለከተ 40

III. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ በህግ መሰረት መከናወኑን እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤ 42

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማስተዳደር የወጡ ህጎችና ደንቦችን መተግበራቸውን በተመለከተ 42

ለሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ 44

ለውጭ አገር ሥራተቋራጮች የሚደረገውን ቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ 48

ለሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ ያስመዘገቧቸው ሀብቶች 50

በስራ ላይ ስለመሆናቸው ክትትል ማድረጉን በተመለከተ 50

የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ 52

በፌደራል እና በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች ያለውን የስራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ በተመለከተ 53

የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ መዘጋጀቱን በተመለከተ 54

በኮንስትራክሽን ዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች የተደረገ ድጋፍን በተመለከተ 55

IV. የሥራ ተቋራጮችንና ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ 58

በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በመመዝገብ ቁጥጥር ማደረጉን በተመለከተ 58

የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አሰሪ መ/ቤቶች ወቅታዊ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ በየጊዜው ማሳወቃቸውን በተመለከተ 59

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ቋት መደራጀቱን በተመለከተ 60

ከባለድርሻ አካላትጋር ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ መደረጉን በተመለከተ 62

ክፍል ሦስት 64

መደምደሚያ (Conclusion) 64

ክፍል አራት 69

የማሻሻያ ሀሳብ (Reccommendation) 69

አባሪ 1፡ i
አባሪ-2፡ ii
አባሪ-3 vii
አባሪ-4፡ viii
አባሪ-5፡ xi
አባሪ-6፡ xiii
አባሪ-7፡- xvii

የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አገራዊ ፍላጎቶችን ማሟላት እንዲችል ቀልጣፋ፣ በተገቢው ወጪ፣ በተያዘለት ጊዜ እና ጥራት የሚፈጸም መሆኑን መቆጣጠር እንዲሁም የዘርፉን ባለሙያዎች፣ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና ፕሮጀክቶችን በመመዝገብ፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በመስጠትና የስራ አፈጻጸም በመቆጣጠር የዜጎችን፣ የአካባቢ ደህነትን እና ጤንነትን ያረጋገጠ እንዲሆን በማድረግ፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን እና ውጤቶችን ጥራት እና ደረጃ በማረጋገጥ ዘርፉን በአህጉር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን የተመቻቸ አሰራር ስርዓት የመዘርጋት፤ የግንባታ ዘዴው ዘመናዊ እንዲሆን የሚያስቻል አገር በቀል የኮንስትራክሽን ተቋማት ብቃትና ቀጣይነትን የሚያረጋግጥ ስትራቴጂ በማመንጨት የቁጥጥር ስራ ይሰራል፡፡ በተለይም በስራ ላይ ያሉ የኮንስትራክሽን ህጎች፣ ኮድና ስታንዳርዶች ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በማሳደግ የተጀመረውን ልማት የማስቀጠል ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

የኦዲቱ ዓላማ የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል አፈፃፀም እና የኮንስትራክሽን ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ **"የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል አፈፃፀም እና የኮንስትራክሽን ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም"** የሚል ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ አራት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱርም፡-

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቋረጡ የፌደራል መንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ በህግ መሰረት መከናወኑን እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

3. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ህጎች መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤
4. የሥራ ተቋራጮችንና ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤የሚሉ ናቸው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of supreme Audit Institutions (IASSAI) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ዝርዝር የክዋኔ ኦዲቱ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል፣የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል አፈፃፀም እና የኮንስትራክሽን ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ከ2013-2015 እና የ2016 ግማሽ አመት ድረስ ያለውን ክንውን እና የተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶችን የኮንትራት ዘመን ሲሆን ለኦዲቱ አሰፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመከልስ እና በመተንተን የክዋኔ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

በክዋኔ ኦዲቱ የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- በፌዴራል በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ የውል ዋጋቸው በድምሩ **ብር10,764,373,751.02 (አስር ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ሰባት መቶ አምሳ አንድ ከ02/100 ብር)** የሆኑ 12 **ፕሮጀክቶች በሁለት ሥራ ተቋራጮች የተያዙ** መሆናቸው፤
- የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት ሊቀንስ የሚችል ሥራ አስቀድሞ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ባለመሰራቱ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመጀመሪያ ውለታቸው ሳይጠናቀቁ በሌላ ጨረታ ወደ ግንባታ የገቡ 13 ፕሮጀክቶች በመንግስት ላይ ያስከተሉት ተጨማሪ ወጪ በድምሩ ብር 16,681,131,031.64 **(አስራ ስድስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺ ሰላሳ አንድ ከ64/100 ብር)** መሆኑ፡
- ፕሮጀክቶች በሚቋረጡበት ጊዜ የፕሮጀክት ባለቤቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እና በባለሥልጣኑም በኩል የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት

ተሰጥቶ ክትትል ባለመደረጉ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ12 ፕሮጀክቶች ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ያልተያዙ ሲሆን የ27 ፕሮጀክቶች ደግሞ በሰነድ ደረጃ ተመዝግበው የተያዙ ቢሆንም ንብረቶቹ በተገቢው ሁኔታ ተጠብቀው ያልተያዙ መሆናቸው፤

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተወሰኑ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የክትትል ስራዎችን ያከናወነ ቢሆንም ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ችግሮችን መፍታት ያልተቻለ መሆኑ፤ በኦዲቱ በታዩ 4 ፕሮጀክቶች የማጠናቀቂያ ሥራ (Finishing) ሲቀራቸው ውለታቸው ተቋርጦ ከ2ዓመት በላይ በመቆየታቸው የጣሪያ መገንጠል እና የጣሪያፍሳሽ ማስወጋጃ (joint Expansion) ሥራ ባለመጠናቀቁ ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፤

❖ በተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት ክፍተት በመኖሩ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ3 ፕሮጀክቶች ብር 471,182,026.54 (አራት መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ሃያ ስድስት ከ54/100 ብር) በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ፤ እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው በ35 ፕሮጀክቶች ብር 1,940,362,449.81 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሃያ ሺ ሶስት መቶ አምሳ አንድ ከ87/100 ብር) በአጠቃላይ የ38 ፕሮጀክቶች ብር **2,411,544,476.35 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ከ41/100 ብር)** የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ያልተወረሰ /ገቢ/ ያልተደረገ መሆኑ፤

❖ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ25 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ (Advance Payments) ብር **3,220,090,230.36** (ሶስት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሚሊዮን ዘጠና ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ከ36/100 ብር) ውስጥ የ6 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ ብር 672,540,236.97 (ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ከ97/100) እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ19 ፕሮጀክቶች ብር 1,795,255,090.20 (አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ አምስት ሺ ዘጠና ከ20/100 ብር) በድምሩ ብር **2,467,795,327.17** (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ ስልሳ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሺ

ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ከ17/100 ብር) ተመላሽ ተደርጎ ለሌሎች የልማት ስራዎች እንዲውል ያልተደረገ መሆኑ፤

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በተደረገ የአካል ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ በናሙና በታዩ ግንባታ ላይ ያሉ 7 ፕሮጀክቶችን የሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች የቅድመ መከላከል ሥራዎችን አሟልተው እየሰሩ አለመሆኑ፤
- ❖ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ላይ ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ ባለመያዙ ናሙናዎችን መርጦ በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው በመስፈርትነት የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በከፊል ሳያሟሉ፣ የማሽነሪ ቴክኒካል ምርመራ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና ሳያድሱ፣ የደረጃ ማሻሻያ ሲያደርጉ የድርጅቱን ተርን ኦቨር ማስረጃ ሳያቀርቡ እና የሌላ ሰው መታወቂያ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤
  - ❖ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች እንዳሉ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ከ14 ሥራ ተቋራጮች ውጪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በምዝገባ መመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል እያደረገ አለመሆኑ፤
  - ❖ በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው የሰው ኃይል፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለተወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን፤ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል በአመታዊ እቅዱ አካቶ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ባለመሆኑ በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች ላይ መለያ(ሰሌዳ) ቁጥር የሌላቸው ማሽነሪዎች የተገኙ መሆናቸው፤

❖ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል የተሟላና በሥራ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የስራ ላይ ስልጠና እያገኙ መሆኑን፣ የሚያቀርቧቸውን ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በክትትልና ቁጥጥር በተረጋገጠ ሪፖርት መሰረት እድሳት እያደረገ አለመሆኑ፤

❖ በፌደራል እና በክልሎች፣በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሁም የፌደራሉ እና የክልሎች ሚና ተለይቶ የተቀመጠ ባለመሆኑ በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ ያወጡ ሥራ ተቋራጮች በድጋሜ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እያወጡ ከአንድ በላይ የሆኑ የብቃት ማረጋገጫዎችን ይዘው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ፤

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ የግል እና የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በደንብ ቁጥር439/2011፣524/2015እናመመሪያ ቁጥር648/2013 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት እንደየምድባቸው መዝግቦ በመያዝ የፕሮጀክቶችን መረጃ ለቁጥጥርና ክትትል ሥራው ግብዓት በሚሆን መልኩ አደራጅቶ ያልያዘ መሆኑ፤

❖ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የአፈጻጸም ደረጃና ወቅታዊ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ አሰሪ መ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ በየስድስት ወር እያሳወቁ ባለመሆኑ ፕሮጀክቶች በውለታቸው መሰረት እየተከናወኑ ያሉ፣ የዘገዩ፣ የተቋረጡ እና የተጠናቀቁ መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ መረጃዎች ተደራጅተው ተይዘው በመረጃው መሰረት ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፤

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ የመረጃ ቋት (database) አደራጅቶ እየያዘ ባለመሆኑ በሀርድ ኮፒ ያሉ የባለሙያዎችና የድርጅቶች ፕሮፋይሎች በብልሽት እየተጋለጡ ያሉ ከመሆኑም በተጨማሪ የኢንዱስትሪው መረጃ በተደራጀ መልኩ ተደራሽ አለመሆኑ፤

❖ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊናበብ የሚችል የቴክኖሎጅ ትስስር እና ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ የሌለው በመሆኑ በሥራ ተቋራጮች የሚቀርቡ

ሰነዶችን በማጣራት እና በፕሮጀክቶች ክትትል በኩል እየገጠሙ ያሉ ችግሮችን ማስቀረት ያልተቻለ መሆኑ፤ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የኦዲት ግኝቶች ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንግሰት በጀት የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ በፕሮጀክቶች መቋረጥ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብና የንብረት ብክነት እና የአገልግሎት አቅርቦት ችግር ከመሰረቱ ሊፈታ የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ የፕሮጀክት ባለቤቶች እና ሥራ ተቋራጮች ላይ የእርምት እርምጃ የሚወሰወድበት አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች መልካም አፈፃፀም ሲባል የመንግስትን ፕሮጀክት የሚሰሩ ተቋራጮች አስቀድመው በወሰዱት ፕሮጀክት ላይ ያሳዩት አፈፃፀም በቀጣይ የሚወዳደሩበት ፕሮጀክት ለማሸነፍ እንደመስፈርት እንዲገባ በማድረግ ተቋራጮችን የያዙትን ፕሮጀክት ጊዜውንና ጥራቱን ጠብቀው በሃላፊነት መስራት ለቀጣይ ሥራዎች ዋስትና መሆኑን እንዲገነዘቡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘርጋ የሚያስችለውን የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆኑ ማዘጋጀት ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር እየተጋለጡ በመሆኑ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ ፕሮጀክቶችን አቋርጠው ከሄዱ ሥራ ተቋራጮች ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (PerformanceGuarantees)ገቢ እንዲደረግ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጠንካራ የክትትል ሥራ መስራት ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጠንካራ ክትትል በማድረግ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ለሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲውል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በመንግስትም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚሰሩ የኮንስትራክሽን ስራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ በመያዝ ተጎጅዎች ወቅቱን የጠበቀ መፍትሔ እንዲያገኙ እና የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊሰራ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥና ደረጃ ሲያድጉ በየደረጃው በአነስተኛ መስፈርትነት የተቀመጠውን የማሽነሪና የተሸከርካሪ፣ የሰው ኃይል፣አመታዊ ተርንኦቨር….ወዘተ ያሚሉ መሆኑ፣ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት የሚቀርቡ የሰነድ ማስጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና የታዩ ክፍተቶችን ለማረም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙ ሁሉም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት እና በሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ላይ ለውጭ አገር ድርጅቶች የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን (የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን እያሳተፉ መሆኑን፣ በዘርፉ የቴክኖሎጅ ወይም ዕውቀት ሽግግር መደረጉን…ወዘተ) በተመለከተ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ እና ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሸከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት፣ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ፣ እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችል፣ ወደ ህገ ወጥ ሥራ

ገብተው ሲገኙም እርምጃ የሚወሰድበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እድሳት ለማድረግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የሰው ኃይል በአካል መኖራቸው በክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ከተረጋገጠ በኋላ እድሳት ሊያድርግ ይገባል፡፡
- ❖ በፌደራል እና በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ተመሳሳይ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ክልሎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙበት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ እንደሀገር መዝግቦ በመያዝ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የፌደራሉን እና የክልሎችን/የከተማ አስተዳደሮች ሚና የለየ፣ የሥራ ተቋራጮችን መብትና ግዴታ በግልፅ ያስቀመጠ አስገዳጅ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ በማዘጋጀት እና ተግባራዊ በማድረግ አሁን እየታየ ያለውን የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ክፍተት፣ ብልሹ አሰራር እና እንደሀገር ያለውን የተደራጀ መረጃ እጥረት እንዲቀረፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት ፕሮጀክቶችን የሚገነቡ አሰሪ መ/ቤቶች ፕሮጀክቶቻቸው ያሉበትን ወቅታዊ ደረጃ የሚያሳይ መረጃ በየ6 ወር የሚያሳውቁበት አሰራር ዘርግቶ መረጃዎችን በመያዝ እና በመረጃው መሰረት ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ መንግስትን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት በመታደግ ተጠቃሚዎችም ከፕሮጀክቶቹ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ ወጥ የመረጃ ቋት (database) አደራጅቶ በመያዝ እራሱም ሆነ ሌሎች የመረጃው ተጠቃሚ አካላት እንዲጠቀሙበት በማድረግ፣ በሀርድ ኮፒ ያሉትን ወደ ሶፍት ኮፒ ቀይሮ በመያዝ እና በሀርድ ኮፒ ያሉትንም ከብልሽት እንዲጠበቁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት አካላት ጋር ዘመናዊ የተክኖሎጅ ትስስር እና ጠንካራ ግንኙነት በማድረግ በጋራ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን መቅረፍ ይኖርበታል፡፡

ክፍል አንድ
መግቢያ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ታሪካዊ ሂደት

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጥንታዊ የግንባታ ቅርሶች የአገሪቱ የኮንስትራክሽን ጥበብ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ መሆኑን የሚያሳዩ ቋሚ ምስክሮች ናቸው፡፡በኋለኛው ዘመን ግን ሥልጣኔው በጦርነት ምክንያት እየጠፋና እየወደቀ ሲሄድ ጥበቡም የሚስፋፋበት ምቹ ሁኔታዎች ባለመኖራቸው የግንባታ ሥራዎች ለረጅም ጊዜያት በበቂ ደረጃ አልነበሩም፡፡በዚህም ምክንያት ሥራው በአብዛኛው በውጪ ባለሙያዎች ድጋፍ ላይ እንዲወድቅ አድርጎት እንደነበረ ይታወሳል፡፡
2. ከመቶ ዓመታት ወዲህ ግን በመጠኑ እየተሻሻለ መጥቶ በአጼ ኃይሌ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በተቋም ደረጃ የገጠር ፕሮጀክቶች ሥራና ሌሎችም በከተማ ውስጥ የግንባታ ኃይል መደራጀት የጀመረ ሲሆን በመቀጠልም በደርግ ዘመን የኮንስትራክሽን ጥያቄው ከፍ እያለ በመምጣቱ በባለሥልጣን ደረጃ ብሎም በሚኒስቴር ደረጃ እንዲቋቋም ሆኗል፡፡
3. በመሆኑም የኢትዮጵያ ህንጻ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 191/1972 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለቤቶች፣ ከተማ ልማት እና ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሆኖ ተቋቁሟል፡፡
4. በመቀጠልም የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 216/1974 ዓ.ም እንዲቋቋም ሲደረግ ቀደም ሲል የተቋቋመውን የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን መ/ቤት በመተካትና ከቤቶች፣ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በመለየት ራሱን ችሎ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በሚል ተቋቋመ፡፡
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሠጠው ኃላፊነት መሠረት የተለያዩ የኮንስትራክሽንና የሬጉላቶሪ ሥራ የሚሠሩ የህንጻና የትራንስፖርት ዲዛይን ባለሥልጣን፣ የህንጻ ዲዛይን ኢንተርፕራይዝ እና ጥቁር ዓባይ ኮንስትራክሽን የመሳሰሉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ድርጅቶችን በማቋቋም በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ የማማከር እና የግንባታ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እንዲሰራ በማድረግ በወቅቱ እየበቀሉ የነበሩትን ኢትዮጵያዊ የሥራ ተቋራጮች በሙሉ እንዲወረሱ አድርጓል፡፡
6. ከደርግ መንግስት ውድቀት በኃላ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከከተማ ልማት ጋር በመሆን በጋራ ሲሰራ ቆይታል፡፡ ይሁን እንጂ የኢፌዲሪ መንግስት የሚከተለው ነጻ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የግል ሴክተሩ መሪ ተዋናይ እንዲሆን በማድረጉና የግል

አማካሪዎችና የሥራ ተቋራጮች እንዲቋቋሙ በመፍቀዱ ኢንዱስትሪው የተሻለ እንቅስቃሴ እንዲያሳይ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ኢኮኖሚው እድገት በማሳየቱና ለውጥ በመምጣቱ ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ተያይዞም መዋቅራዊ ለውጥ በማስፈለጉ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖር በመወሰኑ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሰረት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ራሱን ችሎ ተቋቁሟል፡፡

7. በመንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ላይ የተደረገውን ለውጥ ተከትሎ የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 መሠረት የተቋቋመ ሲሆን ስልጣንና ተግባሩ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 439/2011 መሠረት ተዘርዝሮ ተሰጥቶት ወደ ሥራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡
8. በመጨረሻም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን የሚመራ ራሱን የቻለ ተቋም እንዲኖር በመወሰኑ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ራሱን ችሎ የተቋቋመ ሲሆን በደንብ ቁጥር 439/2011 ያልተካተቱ ተግባራት እንዲካተቱ ተደርጎ በደንብ ቁጥር 524/15 ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቷታል፡፡

የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ስልጣንና ተግባር

የባለሥልጣኑ ራዕይ

9. በ2022 በተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በአፍሪካ ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት

የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ተልዕኮ

10. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተገቢው ወጪ፣ ጊዜ ጥራት መፈጸሙን እንዲሁም የዜጎችን፣ የአካባቢ ደህንነትንና ጤንነትን መጠበቁን በማረጋገጥ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡

የባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ዓላማ

11. ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 524/15 መሰረት የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በተገቢው ወጪ፣ ጊዜ እና ጥራት መፈፀማቸውን በመቆጣጠር ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር ማስቻል፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሚመራበትን ኮድ፣ደረጃ፣ስታንዳርድ እና አሰራር ስርዓቶችን ማዘጋጀት፣በሌሎች አካላት የተዘጋጁትንም ማስፈጸም መቆጣጠር፣
- የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እና ውጤቶችን ጥራት እና ደረጃ ቁጥጥር ማረጋገጥ፣
- የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የዜጎችን፣የአካባቢ ደህንነትን እና ጤንነትን ያረጋገጠ እንዲሆን በቅድመ ግንባታ፣በግንባታ እና በድህረ ግንባታ ወቅት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቀጣይነት ያለው ሀገራዊ ልማት እውን እንዲሆን ማስቻል፣

የባለሥልጣኑ ስልጣንና ተግባር

12.የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 524/15 መሰረት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

- ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ ስታንዳርድና ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣
- በሀገር ደረጃ የወጡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች፣ ደረጃዎችና መመሪያዎች ተግባራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፡፡
- በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘትና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡
- በሀገሪቱ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት እና የመንግስት ፕሮጀክቶችን ይመዘግባል ይቆጣጠራል፡፡
- ለመሰረተ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሥራዎች ግንባታ ሞዴል፣ ስፔስፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓትና ማንዋል ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

- የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች በተገባላቸው በጨረታና ውል መሰረት በዲዛይን፣ በዋጋ፣ በጥራትና በጊዜ ተሰርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል ይቆጣጠራል የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡
- በፌደራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ያለው የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆን የሚያስችል ግልፅነት እና ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሰራር ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡
- ኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን በራሱ ወይም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፡፡
- ኮንስትራክሽን ሥራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይፈትሻል፣ሪፖርት ያቀርባል፣ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይከታተላል፡፡
- የግንባታ ሞዴል ዋጋዎች እና የግምት መስሪያ ቀመሮች ያዘጋጃል፤በዚሁ መሰረት የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለመዘጋጀታቸው ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፡፡
- በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ውስጥ መሥራት ለሚችሉ ሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና በዘርፉ የሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፣ ያግዳል፣ ያሳግዳል፣ ይሰርዛል፣ ወይም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቁጥጥር የሚያገለግል መረጃ ይሰበስባል፤ የመረጃ ቋት ያቋቁማል፤ያጎለብታል፤ ደህንነቱን ይጠብቃል፤ ወቅታዊና ተደራሽ ያደርጋል፡፡
- ኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ያሻሽላል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፡፡
- ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ግብዓቶች መተካት የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡
- በመንግስት የኮንስትራክሽን ሥራዎች ለሚፈጠሩ የውል አለመግባባቶች በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚሰጡ አገልግሎቶች እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ

የሚዘረጋው አሰራር ሥርዓት በአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

- ❖ የመንግስት የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈፃፀም ከጊዜ ከጥራትና ከወጪ አንፃር ክንውኑን ኦዲት ያደርጋል፣በሚገኙ ክፍተቶች የማስተካከያ እርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡
- ❖ ለውጭ ሀገር ዜጎች በሀገራችን ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲሳተፉ ለባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፡፡
- ❖ በተሰጠው ሥልጣን ወሰን የጥናትና ምርምር ሥራዎች ይሰራል፡፡
- ❖ ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ግብዓትና ውጤቶችን ጥራት በመፈተሽ ላብራቶሪ በተመረጡ ቀጠናዎች በማቋቋም አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
- ❖ ለሚሰጠው አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሰረት ክፍያ ያስከፍላል፡፡
- ❖ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል የሚሉ ናቸው፡፡

የባለሥልጣን መ/ቤቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል መዋቅራዊ አደረጃጀት

13.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተርና በሁለት ም/ዋና ዳይሬክተሮች ማለትም በቁጥጥር ዘርፍ እና በምዝገባና ስታንዳርዳይዜሽን ዘርፍ ይመራል፡፡ በዋና ዳይሬክተሩ ስር የዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት፣የሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ፣ ሥነ ምግባር መከታተያ ሥራ አስፈጻሚ፣ የህግ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ፣ የኦዲት ሥራ አስፈጻሚ፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ፣ ሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የግዥ ፋይናንስ ሥራ አስፈጻሚ፣ የብቃትና የሰው ኃብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ፣ የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አስፈጻሚ፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሥራ አስፈጻሚ፣ መስረታዊ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮንስትራክሽን ኦዲትና ኢንስፔክሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ የሚገኙ ሲሆን በምዝገባና ስታንዳርዳይዘሽን ም/ዋና ዳይሬክተር ስር የኮንስትራክሽን ኮድና ስታንዳርድ መሪ ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮንስትራክሽን ሬጉላቶሪ መረጃ ልማትና አናሊስስ መሪ ሥራ አስፈጻሚ እና ኮንስትራክሽን ምዝገባና ብቃት ማረጋገጫ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን የኮንስትራክሽን ሥራዎች ቁጥጥር ዘርፍ

ም/ዋና ዳይሬክተር ስር የኮንስትራክሽን ግጭቶች አፈታት መሪ ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ዲዛይን ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈጻሚ፣ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ግንባታ ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈጻሚ እና የኮንስትራክሽን ግብዓት ቁጥጥር መሪ ሥራ አስፈጻሚ ይገኛሉ፡፡ ዝርዝሩ (በአባሪ-1) ተያይዟል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የሰው ሃይል

14. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተፈቀደው የስራ መደብ 361 ስሆን ክፍት የስራ መደብ 169(46.81%) እና የተሟላው ስራ መደብ 192 (53.19%) ነው፡፡ በሥራ ላይ ካሉ ሰራተኞች ውስጥ 81(42.19%) ሴቶች እና 111(57.81%) ወንዶች ናቸው፡፡የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ሁለተኛ ዲግሪ 33(17.2%)፣የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው126(65.62%)፣ኮሌጅ ዲፕሎማ 8(4.2%) እንዲሁም ከዲፕሎማ በታች ያሉ ሰራተኞች 25(13.02%) ናቸው፡፡

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

15. ባለስልጣን መ/ቤቱ በመቋቋሚያ አዋጅ 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 524/15 የተሰጠውን ተግባር ለማስፈፀም ይረዳው ዘንድ ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2013-2016ግማሽ በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀት እና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

መደበኛ በጀት

	የተመደበ	የተጨመረ (የተቀነሰ)	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ	ልዩነት		ሥራ ላይ የዋለው በ%	ምርመራ
					በመብለጥ	በማነስ		
2013	119,787,560		119,787,56	112,320,783.34		7,486,776.66	93.75	
2014	130,434,768		130,434,768	122,831,761.55		7,603,006.45	94.17	
2015	97,825,000	19,090,168	116,915,168	112,168,668.46		4,746,499.54	95.94	
2016	91,506,000		91,506,000	55,650,247.53			60.82	ግማሽ ዓመት

የቁጥጥር ሥራ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION)

16. የቁጥጥር ሥራ አጠቃላይ የስራ ሂደት መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል።



የኮንስትራሽን የኩባንያዎች እና ባለሙያዎች የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (SYSTEM DISCRIPTION)

17. የኮንስትራሽን የኩባንያዎች እና ባለሙያዎች ምዝገባ የአሰራር ሥርዓት መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



የኦዲቱ ዓላማ

18. የኦዲቱ ዓላማ በፌደራል መንግስት በጀት እየተሰሩ ያሉ ፕሮጀክቶች በውላቸው መሰረት ሳይጠናቀቁ በተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ቁጥጥርና ክትትል ተደርጎ እርምጃ መወሰዱን፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ የስራ ተቋራጮች የሚሰጣቸው ብቃት ማረጋገጫ እና የፕሮጀክቶች ምዝገባ ህግን የተከተለና አገልግሎቱ ቀልጣፋ መሆኑን፣ እንዲሁም በኮንስትራክሽ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሙያ ደህንነትና ጤንነት ህጎችን ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

19. ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ **"የፌደራል መንግስት የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል መደረጉን፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል አፈፃፀም እና የኮንስትራክሽን ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም"** የሚል ነው፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች

20. በተመረጠው የኦዲት አካባቢ ሥር አራት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቋረጡ የፌደራል መንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ በህግ መሰረት መከናወኑን እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤
3. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ህጎች መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤
4. የሥራ ተቋራጮችንና ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤ የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት የመመዘኛ መስፈርት

21. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን አራት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር ስምምነት ላይ ተደርሶ የኦዲት ሥራው እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 439/2011 እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ደንብ ቁጥር 524/2015፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013፣ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የአምስት አመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ /2013-2017 /ዓ.ም፣ የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል፣ ከ2013-2015 ዓ.ም ድረስ ያሉ ዕቅዶችና የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች እና በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተጠኑ ጥናቶች ናቸው፡፡ የመመዘኛ መስፈርቱም በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

22. የኦዲቱ ወሰን የሥራ ተቋራጮች ብቃት ምዘናና ክትትል አፈፃፀም እና የኮንስትራክሽን ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ ከ2013-2015ዓ.ም ድረስ ያለውን ክንውን ሲሆን የተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ደግሞ የኮንትራት የውል ዘመን ነው፡፡

23.የኦዲት ሥራው በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሲሆን በተጨማሪም በናሙና የተመረጡ 41 የተቋረጡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሚገኙባቸው የፕሮጀክት ባለቤቶችን ማለትም የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ የፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት፣ ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፣ ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና ወላይታ ዩኒቨርሲቲ፣የብቃት ማረጋገጫ ከወሰዱ ሥራ ተቋራጮች ውስጥ የ80 ስራ ተቋራጮችን የግል ማህደር በመከለስ፣ የሦስት ክልሎችና የሁለት ከተማ አስተዳደሮች ማለትም የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፣ ሲዳማ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፣ የሐረሪ ክልል የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን እና ድሬዳዋ ከተማ አስተደደር ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ እንዲሁም የአካባቢና የሠራተኛ ደህንነትን እና የሥራ ተቋራጮችን ቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ

በሥራ ላይ ያሉ ሰባት ፕሮጀክቶችን በአካል በመገኘት ለፕሮጀክት ባለቤቶች ወይም ሥራ ተቋራጮች ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን አሰባስቦ በመከለስ፣በመተንተን እንዲሁም አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በመመልከትና ቼክሊስቶችን በመሙላት ኦዲቱን ማከናወን ተችሏል፡፡ዝርዝሩ በአባሪ -3-ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት
የኦዲት ግኝቶች

I. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተቋረጡ የፌደራል መንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምዝገባና ቁጥጥር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

የተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ

24.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው በተቋረጡ ፕሮጀክቶች የታዩ የአፈፃፀም ግድፈቶችን ተከትሎ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ብክነት እና የፕሮጀክቶች ባለቤቶችም ተግባርና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ክትትል በማድረግ ችግሮች እንዲፈቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

25.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- በፌዴራል በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን ይዘው ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤ የውል ዋጋቸው በድምሩ ብር10,764,373,751.02 (**አስር ቢሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰባ ሶስት ሺ ሰባት መቶ አምሳ አንድ ከ02/100 ብር**) የሆኑ 12 **ፕሮጀክቶች በሁለት ሥራ ተቋራጮች የተያዙ** መሆናቸው፤ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡
    - ✓ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የውል ዋጋቸው ብር 5,667,294,618.05 (**አምስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አራት ሺ ስድስት መቶ አስራ ስምንት ከ05/100**) የሆነ 7 ፕሮጀክቶች ማለትም 3 ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ 3 ከፌዴራል ህንፃዎች ግንባታ ጽ/ቤት እና 1 ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ተይዘው የተቋረጡ መሆናቸው፤
    - ✓ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የውል ዋጋቸው ብር ብር 5,097,079,132.97 (**አምስት ቢሊዮን ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ሰባ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ከ97/100**) የሆነ 5 ፕሮጀክቶች

ማለትም 1 ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ፣ 2 ከፌዴራል ህንፃዎች ግንባታ ጽ/ቤት፣ 1 ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ እና 1 ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ተይዘው የተቋረጡ መሆናቸው፤

- ➢ በሀገሪቱ ያሉ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በፍጥነት ተመልሰው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 13 ፕሮጀክቶች ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ ቢሆንም 28ቱ ግን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ➢ ፕሮጀክቶች በሚቋረጡበት ጊዜ የፕሮጀክት ባለቤቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እና በባለሥልጣኑም በኩል የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል ባለመደረጉ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ12 ፕሮጀክቶች ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ያልተያዙ ሲሆን የ27 ፕሮጀክቶች ደግሞ በሰነድ ደረጃ ተመዝግበው የተያዙ ቢሆንም ንብረቶቹ በተገቢው ሁኔታ ተጠብቀው ያልተያዙ መሆናቸው፤
- ➢ የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት መኖሩ፤ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ 13 ፕሮጀክቶችን መሰረት በማድረግ ፕሮጀክቶቹ በመጀመሪያ ውለታቸው ተገንብተው ባለመጠናቀቃቸው በመንግስት ላይ ያስከተሉትን ተጨማሪ ወጪ በድምሩ ብር 16,681,131,031.64 **(አስራ ስድስት ቢሊዮን ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺ ሰላሳ አንድ ከ64/100)** መሆኑ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

  - ✓ **በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንበታ የገቡ 4 ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው የውል ዋጋ ብር 3,947,579,832.16 ሲሆን በድጋሚ ወደ ውለታ የተገባው የገንዘብ መጠን ደግሞ ብር 12,436,021,306.72 ሲሆን በሁለቱ ውለታዎች መካከል የሚታየው የገንዘብ ልዩነት በድምሩ **ብር 8,488,441,474.56** መሆኑ፤
  - ✓ **በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ጽ/ቤት** በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንበታ የገቡ 4 ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው የውል ዋጋ በድምሩ ብር

4,132,455,149.77 ሲሆን በድጋሚ ወደ ውለታ የተገባው የገንዘብ መጠን ደግሞ ብር 10,591,566,388.14 ነው፡፡ በሁለቱ ውለታዎች መካከል የሚታየው የገንዘብ ልዩነት በድምሩ ብር **6,459,111,238.37** መሆኑ፤

- ✓ **በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 8 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንባታ የገቡ 2 ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው የውል ዋጋ ብር 147,413,726.80 ሲሆን በድጋሚ ወደ ውለታ የተገባው የገንዘብ መጠን ደግሞ ብር 1,058,711,937.31 ነው፡፡ በሁለቱ ውለታዎች መካከል የሚታየው የገንዘብ ልዩነት በድምሩ **ብር 911,298,210**.51 መሆኑ፤
- ✓ **በወላይታ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተመልሰው ወደ ግንበታ የገቡ 3 ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው የውል ዋጋ ብር 401,964,078.92 ሲሆን በድጋሚ ወደ ውለታ የተገባው የገንዘብ መጠን ደግሞ ብር1,224,244,187.06 ነው፡፡በሁለቱ ውለታዎች መካከል የሚታየው የገንዘብ ልዩነት በድምሩ **ብር 822,280,108.14** መሆኑ ታውቋል፡፡

አጠቃላይ ፕሮጀክቶቹ የተጀመሩበት ጊዜ፤ መጠናቀቅ የነበረባቸው ጊዜ፣ የተቋረጡበት ጊዜ፣ የተቋረጡበትን ምክንያት፣ ፕሮጀክቱ ሲቋረጥ ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ያሉበትን ሁኔታ እና የፕሮጀክቶች መቋረጥ ያስከተለውን ተጨማሪ ወጪ የሚያሳይ ሠንጠረዥ በአባሪ 4 ፣ 5 እና 6 ተያይዟል፡፡

26. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በቁጥጥር ወቅት በምንገናኝበት ጊዜ ከአሠሪ ባለ በጀት መ/ቤቶች ጋር በነበረን ክትትል ፕሮጀክቶቹ ጉዳያቸው በፍ/ቤት የተያዘ መሆኑን በመግለጽ የክስ ሂደቶቹን የሚያሳዩ ሰነዶች ያቀርቡ እና በህግ የተያዙ ስለሆነ የቁጥጥር ሥራው የትኩረት አቅጣጫ እምብዛም አልነበሩም፡፡ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን በቁጥጥር ወቅት ሲያገኝ እያንዳንዱ አሰሪ መ/ቤት ህግና መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊውን ሂደት በማከናወን ፕሮጀክቶቻቸውን በሌላ አማራጭ እንዲያጠናቅቁ ግብረመልስ በማዘጋጀት ለአሰሪው መ/ቤት ከመስጠት ባለፈ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያሳውቅ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

27. እንዲሁም የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ተመልሰው ወደ ውለታ ሲገቡ የታየውን ከፍተኛ የገንዘብ ልዩነት በተመለከተም የባለሥልጣን መ/ቤቱ ፍላጎት አይደለም፤ባለሥልጣን መ/ቤቱ አሰሪ መ/ቤቶች ፕሮጀክት እንዲያቋርጡ እና በሌላ ተቋራጭ እንዲያስጨርሱ እንደ መጀመሪያ አማራጭ ሀሳብ አያቀርብም፣ ይልቁንም ፕሮጀክቶች በዚያው ተቋራጭ እንዲጠናቀቁ ያሉትን የውል አማራጮች እንደ ዋጋ ማስተካከያ፣ እንደ የጊዜ ማራዘሚያ በመስጠት ወይም ሌሎችን አካላት ማለትም የገንዘብ ሚኒስቴርን፣ የግዥና ንብረት ባለስልጣንን በማማከር ሌሎች አማራጮች ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ለባለቤት መ/ቤት እድል ሰጥተናል፡፡

28. በሌላ በኩል የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድጋሚ ጨረታ በማውጣት እንዲሰራ መደረጉ ድፍን ባለ መልኩ ብክነት እንደሆነ መታሰቡ አግባብ አይመስለንም ምክንያቱም የፕሮጀክቶች አተገባበር በራሱ በውል የሚመራ ሲሆን ውለታቸው መጀመሪያ በምን አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደተቋረጠ ማለትም በአሰሪው መ/ቤት ፍላጎት ወይም በተቋራጭ ፍላጎት ወይም ከአቅም በላይ አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች መሆኑ ቢለይና ቢታይ ጥሩ ነው፣ ይህንንም በተመለከተ ውለታውን ለማስተዳደር የመንግሥትን በጀት የሚያስተዳድረው አሰሪ መ/ቤት ውል ማቋረጡ በተቋራጭ ክፍተት መሆኑን ማረጋገጥ ከቻለ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናውን በወቅቱ በመውረስ ሊከሰት ያለውን ብክነት የመቀነስ ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህንን የመሳሰሉ በኢንዱስትሪው የሚታዩ የውል ጥሰቶችን እና ብክነትን ለመቀነስ ተጠያቂነትን ለማስፈን በተቋሙ የኦዲትና ኢንስፔክሽን የሥራ ክፍል አደራጅቶ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ጀምሯል፡፡

29. ፕሮጀክቶች ሲቋረጡ ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ስለመያዛቸው ክትትል መደረጉን በተመለከተ በውል ጥሰት የሚደረግ የውል ማቋረጥ ከሆነ በውለታ መቋረጥ ወቅት ያለውን አሰራር በአጠቃላይ የውል ሁኔታ ከአንቀጽ 20 እስከ አንቀጽ 25 ባለው መሠረት መከናወኑን ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ያከናውናል፡፡ ይሁን እንጂ ከውለታ መቋረጥ በኋላ ያለውን የንብረት አያያዝን በተመለከተ ለወደፊት ትኩረት ተሰጥቶበት መሥራት እንደሚያስፈልግ የተቀበልነው ሀሳብ ነው፡፡

30. በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤታችን ፕሮጀክቶችን ለቁጥጥር በሚመርጥበት መስፈርት ውስጥ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ምክረ ሀሳቡን ወስደን የምናስተካክል ይሆናል፡፡ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ

በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል ህግ የለም፡፡ ነገር ግን እያበላሹ ሲሄዱ ክትትል ማድረግ አለብን፡፡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንደ ገንዘብ ሚኒስቴር፤ ፕላን ሚኒስቴር ፣ ግዥ ኤጀንሲ የዚህ ሊሳተፉ ይገባል በማለት ገልፀዋል፡፡

31. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ግብረ መልስ የተሰጣቸው 8 ፕሮጀክቶች ላይ እርምጃ እስከመውሰድ የተደረገ ክትትል ባለመኖሩ፣ እንዲሁም በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች በተለይም በዩኒቨርሲቲዎች ፕሮጀክቶችን በመጀመሪያ ዋጋቸው ከማስጨረስ ይልቅ ማቋረጥና ወደ ሌላ ጨረታ መሄድ በየጊዜው እየጨመረ ያለውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር እንደወሳኝ መፍትሔ የመውሰድ አዝማሚያ የታየ በመሆኑ፤ እና ባለሥልጣን መ/ቤቱ ተቋራጮች ፕሮጀክቶችን አፈፃፀማቸው ሳይታይ በላይ በላይ የሚሰጣቸው መሆኑንና ያለውን ስጋት ግንዛቤውስጥ በማስገባት የአሰራር ሥርዓትና የህግ ማዕቀፍ እንዲወጣ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡
32. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት እና በፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ላይ የሚፈጥረውን ጫና የሚቀንስ ስራ በሁሉም በተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ባለመሰራቱ የፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ከፕሮጀክቱ ወቅቱን የጠበቀ አገልግሎት እንዳያገኙ እና መንግስት ለከፍተኛ ተጨማሪ ወጭ እንዲዳርግ ከማድረጉም በተጨማሪ ፕሮጀክቶች ሲቋረጡ በሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ተይዘው ፕሮጀክቱ ወደሥራ ሲገባ ተጨማሪ ግብዓት እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡
33. እንዲሁም የመንግስትን ፕሮጀክት የሚሰሩ ተቋራጮች ተጨማሪ ፕሮጀክቶች ሲሰጣቸው አፈፃፀማቸው እንደመስፈርት ባለመቀመጡ የሀገሪቱን ፕሮጀክቶች በውስን ተቋራጮች እንዲከናወን ከማድረጉም ባሻገር የጀመሩትን ስራ በመልካም አፈፃፀም በጊዜውና በጥራት መጨረስ በቀጣይ ለሚወዳደሩበት ፕሮጀክት መሰረት እንደሆነ በመቁጠር ሃላፊነተታቸውን እንዳይወጡ ከማድረጉም በላይ ተቋራጮች በተለያየ ምክንያት ከገቢያው ሲወጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ያለባለቤት እንዲቀሩ በማድረግ የሀገርና የህዝብ ገንዘብና ንብረት እንዲባክን አድርጓል፡፡

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ከብልሽት መጠበቃቸውን በተመለከተ

34.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ክትትል በማድረግ ወደ ውለታ የሚገቡበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

35.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተወሰኑ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የቁጥጥርና ክትትል ስራዎችን ያከናወነ ቢሆንም ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ሥራ አለመሰራቱ፤ ለአብነት ያህል በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የፋና ህይወት ጠቅላላ ሆስፒታል፤ በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የዳዬ ካምፓስ ሁለት የተማሪዎች ማደሪያ፣ አንድ መጋዘን፣ ሁለት የሠራተኛ መኖሪያ እና የአንድ ካፍቴሪያ ፕሮጀክቶች የማጠናቀቅያ ሥራ (Finishing) ሲቀራቸው ተቋርጠው ከ2ዓመት በላይ በመቆየታቸው በጣሪያ መገንጠል እና የጣሪያ ፍሳሽ ማስወጋጃ (joint Expansion) ባለመገጠሙ ምክንያት ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

36.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ባለስልጣኑ እንደ መፍትሔ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ያደርግ የነበረው እንቅስቃሴ በተለያየ ምክንያቶች ውለታቸው ተቋርጦ ወይም ውላቸው ሳይቋረጥ ቆመው ረጅም ጊዜ የሆናቸው ፕሮጀክቶች ወደ ቀጣይ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የጥራት ፍተሻዎችን እንዲያከናውኑ በግብረመልስ እያሳወቁ መቆየቱ፣ በግብረመልሱ ይዘት ውስጥ የግንባታዎቹ ውለታ ሳይቋረጥ ከውል ውጭ የሆኑ እና የቆሙ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያ ህይወት እንዲኖራቸው እና ተዋዋይ ወገኖች ወደ ውል ግዴታቸው ውስጥ እንዲገቡ ምክር እየተሰጣቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የጥራት ችግሮች የታዩባቸውን ፕሮጀክቶች በላቦራቶሪ ፍተሻ ጥራታቸው ካልተረጋገጠ ወደ ሥራ እንዳይገቡ እያደረገ መሆኑ፣ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በክስ ሂደት ላይ መሆናቸው፤ በተለያዩ ምክንያቶች የቆሙ ፕሮጀክቶች ምክንያቶቻቸው ተለይተው ፕሮጀክቶቹ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ እንዲፈጥሩ ለባለበጀቱ መ/ቤት ምክረ-ሀሳቦችን በግብረመልስ ደብዳቤ እየተሰጣቸው የነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

37.በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅትም ግኝቱ ትክክል ነው፣ ለማሳያ የተጠቀሱትን ፕሮጀክቶች በተደጋጋሚ ሰርተናል ነገር ግን እኛ መፍታት አንችልም ጉዳዩ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ መፍታት እንዳለበት ታሳቢ መደረግ ይኖርበታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

38.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ከታዩ 41 ፕሮጀክቶች ውስጥ ባለሥልጣኑ ክትትል አድርጎ ግብረመልስ የሰጠባቸው ፕሮጅቶች በወላይታ ዩኒቨርሲቲ ለታዩ 7 ፕሮጀክቶች እና በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ አንድ ፕሮጀክት ብቻ ሆኖ እያለ ሁሉንም ፕሮጀክቶች ክትትል ባደረገ መልኩ አብዛኛዎቹ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በክስ ሂደት ላይ ናቸው ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ በተመለከተ በክስ ሂደት ላይ ያሉት ቀድሞ ፕሮጀክቶችን ይሰሩ የነበሩ ሥራ ተቋራጮች ናቸው እንጅ ፕሮጀክቶቹ ታግደው የቆሙ ባለመሆኑ የጥራት ችግር ሳይገጥማቸው ወደ ሥራ እንዲገቡ ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር በመሆን ክትትል እንዳያደርግ የሚከለክል ጉዳይ የሌለ በመሆኑ፤ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚሰጣቸው ግብረ መልሶች ምንያህል ተጨባጭ ፍሬ አፍርተዋል የሚለውን ጉዳይ መርምሮ ግብረ መልስ ከመስጠት የዘለለ እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን የሚፈታበት አቅጣጫ ማስቀመጥ መቻል ያለበት በመሆኑ፤ በምሳሌነት ከተጠቀሱት ውስጥ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሀረር ህይወት ፋና ሪፌራል ሆስፒታል ባለሥልጣኑ የሰጠውን ግብረ መልስ መሰረት ተደርጎ ከተቋረጠ በኋላ የጥራት ችግር እየገጠመው የሚገኝ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ወደ ግንባታ እንዲገባ ያልተደረገ መሆኑ፤እንዲሁም ሌሎች የተጠቀሱ ፕሮጀክቶች ላይ ስራ የተሰራ ቢሆንም አሁን በተጨባጭ በሀገሪቱ ላይ እየደረሰ ካለው የፕሮጀክቶች የጥራት ችግር አንፃር አመርቂ ሥራ ተሰርቷል ለማለት ያስቸግራል፡፡

39.ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ሥራዎች አለመሰራታቸው ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ተጋልጠው አገልግሎት መስጠት ማይችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ እና ለተሰራው ስራ የወጣው ወጪ ሙሉ በሙሉ እንዲባክን በማድረግ ለተጨማሪ ወጪና ብክነት ይዳርጋል፡፡

ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና አፈፃፀም በተመለከተ

40.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ገቢ መደረጉን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

41.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ተመርጠው ማስረጃቸው ከተከለሱ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ3 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ ብር 471,182,026.54 (አራት መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ሃያ ስድስት ከ54/100 ብር) እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ35 ፕሮጀክቶች ብር1,940,362,449.81 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሃያ ሺ ሶስት መቶ ሃምሳ አንድ ከ87/100 ብር) በአጠቃላይ የ38 ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር **2,411,544,476.35** (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ከ41/100 ብር) የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) ከሥራ ተቋራጮች ጋር የተገባውን ውል መሰረት ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ያልተወረሰ /ገቢ/ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ተገልፃል፡-

- **በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ9 ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 1,301,857,648.25 (አንድ ቢሊዮን ሶስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ስድስት መቶ አርባ ስምንትከ24/100) በውሉ መሰረት ያልተወረሰ/ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ተመልክቷል፡፡
  - ✓ **አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ** መንገድ ፕሮጀክት ከሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ ጋር ውል የተገባው ብር **117,823,523.099** የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ጋሴራ-ጊኒር** መንገድ ፕሮጀክት ከአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር **84,160,201.92** የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **አቦምሳ-አሰኮ-ዲቡወንዝ** ኮንትራት-1 መንገድ ፕሮጀክት ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር

99,172,199.78 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **ዲቡወንዝ-በደይ-ጨለለቃ** ኮንትራት-2 መንገድ ፕሮጀክት ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 72,562,142.82 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ሮቤ-ሴሩ መንገድ ፕሮጀክት** ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ብር 99,318,149.538 እና ከዩኒፕሬሳ እስፓ ብር 232,294,839.55 ውል የተገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ወራቤ-ቦጆበር መንገድ ፕሮጀክት** ከየማነ ግርማይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ብር 45,844,565.00 እና ከማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ብር 79,500,000.00 ውል የተገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ፍሰሃ-ገነት-ኬሌ-ነደሌ ኮንትራት-1** መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ሎት-1ከሻንዶንግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ(ቻይና ናሽናል ኬሚካል ኮምዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ግሩፕ) ጋር ውል የተገባው ብር 161,200,686.68 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ጅማ-ጭዳእናሶዶ-ሳውላ(ድንኬ-ሳውላ)**መንገድማሻሻያ ፕሮጀክት፡ሎት3፡ከቤጅንግ አርባን ኮንስትራክሽን ግሩፕ ኮ. ሊትድ ጋር ውል የተገባው ብር 103,595,581.18 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ጨሉሴ-ሶያማ(ፍሰሃ ገነት ኮንትራት** -2) ከቻይና ሬልዌይ 14ኛ ቢሮ ግሩፕ.ኮ.ሊትድ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ጋር ውል የተገባው ብር 206,385,758.68 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ **በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ጽ/ቤት** በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 738,382,441.85(ሰባት መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን

ሦስት መቶ ሰማኒያ ሺ አራት መቶ አርባ አንድ ከ85/100) በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **የቀድሞው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች(በአሁኑ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር)** **የቢሮ ግንባታ** ፕሮጀክት ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 120,719,570.29 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የሲቪል አቬንሽ ዋና መ/ቤት** የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ከቢሃ ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 43,884,960.85 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር** የግንባታ ፕሮጀክት ከአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 149,720,255.03 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር** የቢሮ እና የዲፕሎማቶች መኖሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ከአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 113,549,049.09 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የፌዴራል ዳኞች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ** ፕሮጀክት ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 91,827,853.01 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የከፍተኛ ባለሥልጣናት መኖሪያ ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት** ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል ከተገባው ብር 15,407,950.75 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት** ግንባታ ፕሮጀክት ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ጋር ውል የተገባው ብር 203,272,802.83 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- **በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 6 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 148,447,776.94(አንድ መቶ አርባ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶአርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ከ94/100) በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡-
  - ✓ **የዘመናዊ ገራጅ ግንባታ ፕሮጀክት** ከቢሃ ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 9,450,518.47 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የኤሌክትሪክ ስቴሽን ግንባታ ፕሮጀክት ከኤልቴል** ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 6,750,704.14 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ኬሚካል ስቶር ግንባታ ፕሮጀክት** ከሞውልድ ኢስማኤል ስራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 715,207.53 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ጉርሱም ምርምር ማዕከል ግንባታ ፕሮጀክት** ከበቀለ ቡርሳ ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 1,502,564.74 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የህይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት** ከአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 127,706,727.07 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የፅኑ ህሙማን ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት** ከያሬድ ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 2,322,054.99 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- **ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 5 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 57,568,611.11(ሃምሳ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ ስድስት መቶ አስራ አንድ ከ11/100) በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡-
  - ✓ **የአጥር እና ምድረ-ግቢ ግንባታ ፕሮጀክት** ከዳዊት ሀ/ማርያም ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 3,643,052.23 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የተማሪዎች መኖሪያ ጥገና ፕሮጀክት ኮንትራት**1እና2 ከየት–ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 2,309,411.35 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት** ከ3ኤም ኢንጅነሪንግ ጋር ውል የተገባው ብር 17,044,467.35 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት ከአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 34,571,680.18 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ **በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 4 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 111,980,572.92 (አንድ መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ አራት መቶ ሰባ አራት ከ98/100) በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡-

- ✓ የጤና ካምፓስ የተማሪዎች መማሪያ፣ ማደሪያ፣ካፍተሪያ እና የሰራተኛ መኖሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ከፍልንትስቶን ጋር ውል የተገባው ብር 17,028,423.00 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በዳዬ ካምፓስ የተማሪዎች ማደሪያ፣ የመጋዘን፣ የሰራተኛ መኖሪያ እና የካፍተሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ከተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ጋር ውል የተገባው ብር 65,021,595.85 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የቴክኖሎጅ ካምፓስ የቤተ መፅሐፍት፣ የተማሪዎች መመገቢያዎች እና የመጋዘን ግንባታ ግንባታ ፕሮጀክት ከመስኮን ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 29,363,693.79 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ የወንዶገነት ካምፓስ የአጥር ግንባታ ግንባታ ፕሮጀክት ስንታየሁ ወ/ጊወርጊስ ጋር ውል የተገባው ብር 566,860.28 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ **በወላይታ ዩኒቨርሲቲ** በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 53,307,425.29(ሃምሳ ሦስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባት ሺ አራት መቶ ሃያ አምስትከ29/100) በውሉ መሰረት ያልተወረሰ/ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡-

- ✓ **ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የአጥር ግንባታ** ፕሮጀክት ከአዱኛ ለማ ጋር ውል የተገባው ብር 257,730.41 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የመምህራን መዝናኛና** ሽንት ቤትና ሻወር ግንባታ ፕሮጀክት ከማርቆስ መንገሻ ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 681,630.88 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **በዳውሮ ታርጫ የመማሪያ ክፍሎች** ግንባታ ፕሮጀክት ከብርሃን ጠቢያው ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 8,012,686.33 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **በዋና ግቢ የአመራሮች መኖሪያ** ግንባታ ፕሮጀክት ከጌታቸው አባይ ጋር ውል የተገባው ብር 4,158,979.79 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የዳውሮ ታርጫ የአስተዳደር ህንጻ፤የተማሪዎች** ክሊንክ እና የተማሪዎች ማደሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ከዮሐንስ ኃይሌ ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 13,684,451.39 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **በዋና ግቢ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ** ፕሮጀክት ከጥለሁን አበበ ሥራ ተቋራጭ ጋር ውል የተገባው ብር 11,394,099.23 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **በዋና ግቢ የተማሪዎች ማደሪያ** ግንባታ ፕሮጀክት ከእቴቴ ኮንስትራክሽን ጋር ውል የተገባው ብር 15,117,847.26 የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

አጠቃላይ ዝርዝሩ **በአባሪ 7** ተያይዟል

42.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ተቋማችን የቁጥጥር ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ሊያገኝ ይችላል፤ በመሆኑም ውል የተቋረጠበትን አግባብ ከውለታ ሰነዳቸውና ከተያያዥ የህግ ሠነዶች አንፃር በመገምገም አስፈላጊውን ምክረ ሀሳብ ለአሰሪው መ/ቤት ያቀርባል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ሳያሳድሱ ወይም ለሚመለከተው የዋስትና ሰጪ ተቋም ሳያሳውቁ የዋስትናው ጊዜ ያለፈባቸው ከሆነ ወደ ክስ በመሄድ በህግ አግባብ እንዲጨርሱ ምክረ ሃሳብ እያቀረቡ እንደሆነ፤ በግብረመልሱ ይዘት ውስጥ የግንባታዎቹ ውለታ ሳይቋረጥ ከውል ውጭ የሆኑ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያ ህይወት እንዲኖራቸውና ተዋዋይ ወገኖች ወደ ውል ግዴታቸው ውስጥ እንዲገቡ ማለትም

የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናቸውን እንዲያሳድሱ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ የጊዜ ማራዘሚያ እንዲሰጣቸው ምክረ ሀሳብ እየተሰጣቸው እንደሆነ፣ በውለታ ጊዜ ውስጥ ያሉ ከሆነ ዋስትናውን ከሰጠው ተቋም ጋር በመነጋገር የዋስትናውን ገንዘብ እንዲያስመልሱ ለባለቤት መ/ቤቶች በግብረመልስ እንደሚያሳውቁ ገልጸው ማሳያ ያሏቸውን ማስረጃ ለኦዲቱ አቅርበዋል፡፡

43.በተጨማሪም አብዛኛዎቹ በናሙና የታዩ ፕሮጀክቶች በክስ ሂደት ላይ የነበሩና ባለስልጣኑ ከመቋቋሙ በፊት የነበሩ፣ በተቋማችን ለቁጥጥር ሥራ ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያልነበሩ እንዲሁም በፍርድ ቤት ክስ ሂደት ላይ የደረሱ ነበሩ፣ ይህንን ስንረዳ በፍርድ ቤት የተያዙ ፕሮጀክቶችን መቆጣጠር ስለማይመለከተን በቁጥጥር ሂደታችን እምብዛም የትኩረት አቅጣጫ አልነበረም፣ ስለሆነም የኦዲት ቡድኑ ይህንን ተረድቶ ከዚህ ጋር በተገናኘ የተያዙ የኦዲት ግኝቶች ሊሰረዙ ይገባል፡፡ እንዲሁም በኦዲት ቡድኑ የታዩት የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን መረጃ በመያዝ ተቋማች ወደ ሥራ በመግባት የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን የቅድመ ክፍያና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ያለበትን ሁኔታ አጣርቷል፤በዚሁ መሰረት

- **በፌዴራል መንግስት ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት** ባለቤትነት ይከናወኑ የነበሩ እና ውለታቸው ከተቋረጡት 7 ፕሮጀክቶች ውስጥ በ7 ፕሮጀክቶች ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ገቢ ያልተደረገ መሆኑ የ6 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እስከአሁን የተያዘ ሲሆን ከ7 ውስጥ 1 ፕሮጀክት በመንግሥት ሥራ ተቋራጭ የተያዘ በመሆኑ ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም በተመለከተ የመንግሥት ለመንግሥት ድርድር ላይ መሆኑ፣
- በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ተርጫ ካምፓስ ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 4 ፕሮጀክቶች ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያና መልካም ሥራ አፈፃፀም ዙሪያ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው አስከአሁን የተያዘ መሆኑና 3 የቅድመ ክፍያ ዕዳቸውን ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸው ያልተከሰሱ መሆኑ፣
- **በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** እየተገነቡ ከነበሩትና ውለታቸው ከተቋረጡት 10 ፕሮጀክቶች ውስጥ 6 ፕሮጀክቶች ባልተመለሰ ቅድመክፍያና ገቢ ባልተደረገ መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እስከአሁን የተያዘ መሆኑ፣ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ይገነቡ

የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 1 ፕሮጀክት በፍርድ ቤት ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ ሌሎቹ በተቋማችን በተሰጠ አስተያየት መሠረት ከዋስትና ሰጪ ተቋማት ጋር ድርድር በማድረግ 2 ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ የመለሱበትና ሌሎቹ ወደ ክስ ሂደት ለመሄድ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑ፣

- **በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ 8 ፕሮጀክቶችን ውስጥ 6 ባልተመለሰ ቅድመ ክፍያና መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘ ሲሆን 1 ውለታው እስከ ግንቦት 2014 ዓ.ም ተራዝሞ በውል ውስጥ ያለ መሆኑ 1 ግደታውን በመወጣቱ ውሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑ፣
- **በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ 4 ፕሮጀክቶችን ውስጥ ያልተመለሰ ቅድመክፍያ 1 ፕሮጀክት ባልተመለሰ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ ሲሆን 1 ፕሮጀክት ቅድመክፍያ የወሰደውን እንዲመልስ ዋስትናውን ከሰጠው ተቋም ጋር እየተሰራ ይገኛል፤ በማለት አብራርተዋል፡፡

44. በተጨማሪም በኦዲቱ የመውጫ ስብሰባ ወቅት በኦዲቱ የታዩ ከላይ የተዘረዘሩ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ መሆናቸውንና ክትትልም በማድረግ ገንዘቡን ማስመለስ እንደማይቻል፤ ነገር ግን ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ወደ ሥራ እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

45.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በናሙና የታዩ ከላይ የተዘረዘሩ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ መሆናቸውንና ክትትል በማድረግ ገንዘቡን ማስመለስ እንደማይቻል የተገለፀ ቢሆንም ከሁለት ፕሮጀክቶች ውጭ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤ በተቋሙ በተደረገ ክትትልና ግብረ መልስ እስካሁን የተመለሰ የመልካም ሥራ ዋስትና ስለመኖሩ ማስረጃው ያልቀረበ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

46.ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተደራጀና የተቀናጀ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ባለማከናወኑ መንግስት ከተቋረጡ ፕሮጀክቶች መሰብሰብ የነበረበትን ገንዘብ በመሰብሰብ በወቅቱ ወደመንግስት ገቢ እንዳይሆን በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያጣ አድርጓል፡፡

ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ እንዲደረጉ ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

47.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ ስለመደረጋቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

48.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ25 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ (Advance Payments) ብር **3,220,090,230.46** (ሦስት ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሚሊዮን ዘጠና ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ከ46/100 ብር) ውስጥ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ የ6 ፕሮጀክቶች ብር 672,540,236.97 (ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት ከ97/100 ብር) እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ19 ፕሮጀክቶች ብር 1,795,255,090.20 (አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ አምስት ሺ ዘጠና ከ20/100 ብር) በድምሩ **ብር 2,467,795,327.17** (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ ስልሳ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሶስት መቶ ሃያ ሰባት ከ17/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

- **በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** በናሙና ከታዩ 10 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ9ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 1,997,273,584.08 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ሺ አምስት መቶ ሰማኒያ አራት ከ08/100 ብር) ውስጥ በድምሩ ብር**1,749,443,422.46** (አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ አርባ ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሶስት ሺ አራት መቶ ሃያ ሁለት ከ46/100) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ተመልክቷል፣
  - ✓ **አጣጥ ማዞሪያ-ጉንችሬ-ኮሴ-ጌጃ-ሌራ መንገድ ፕሮጀክት** ለሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 233,059,918.90 (ሁለት መቶ ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን አምሳ ዘጠኝ ሲ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ከ90/100 ብር) ውስጥ ብር**180,051,945.97 (አንድ መቶ ሰማንያ ሚሊዮን አምሳ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት ከ97/100 ብር)** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ጋሴራ-ጊኒር መንገድ ፕሮጀክት** ለአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 168,320,403.80 (አንድ መቶ ስልሳ ስምንት

ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ሺ አራት መቶ ሶስት ከ80/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **አቦምሳ-አሰኮ-ዲቡወንዝ ኮንትራት-1 መንገድ ፕሮጀክት** ለተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር** 176,823,088.20 (አንድ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃያ ሶስት ሺ ሰማንያ ስምንት ከ20/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ዲቡወንዝ-በደይ-ጨለለቃ ኮንትራት-2 መንገድ ፕሮጀክት** ለተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 129,109,555.18 (አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ አምሳ አምስት ከ18/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ሮቤ-ሴሩ መንገድ ፕሮጀክት** ለተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽንኃ.የተ.የግ ማህበር **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 89,609,174.02 (ሰማንያ ዘጠኝ ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰባ አራት ከ02/100 ብር) እና ለዩኒፕሬሳእስፓ **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር **207,719,848.21** (ሁለት መቶ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ አርባ ስምንት ከ21/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ወራቤ-ቦጆበር መንገድ ፕሮጀክት** ለየማነ ግርማይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 91,689,130.00 (ዘጠና አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ብር) እና ለማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 159,000,000.00 (አንድ መቶ አምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር) ውስጥ ብር **104,533,615.07** (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ስድስት መቶ አስራ አምስት ከ07/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ፍሰሃ-ገነት-ኬሌ-ነደሌ** መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ሎት-1 ለሻንዶንግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ (ቻይና ናሽናል ኬሚካል ኮምዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ግሩፕ) የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር **325,404,036.76 (ሶስት መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አራት ሺ ሰላሳ ስድስት ከ76/100 ብር)** በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **ጅማ-ጭዳእናሶዶ-ሳውላ (ድንኬ-ሳውላ)** መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ሎት3፡ ለቤጅንግ አርባን ኮንስትራክሽን ግሩፕ ኮ.ሊ.ትድ ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ

ብር189,151,930.64 (አንድ መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ አምሳ አንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ከ64/100 ብር) ውስጥ ብር 104,320,690.45 (አንድ መቶ አራት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ሺ ስድስት መቶ ዘጠና ከ45/100 ብር) በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **ጨሉሴ-ሶያማ(ፍሰሃ ገነት ኮንትራት -2)** ለቻይና ሬልዌይ 14ኛ ቢሮ ግሩፕ.ኮ.ሊ.ትድ ኢ.ትዮጵያ ቅርንጫፍ የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር **227,386,499.05 (ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰማንያ ስድስት ሺ አራት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ05/100 ብር)** በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ **በፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ጽ/ቤት በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ** ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ4 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 751,587,850.17(ሰባት መቶ ሃምሳ አንድ ሚሊዮን አምስት ሰማኒያ ሰባት ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ ከ17/100) ውስጥ በድምሩ ብር 597,819,881.51(አምስት መቶ ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ አንድ ከ51/100) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡-

- ✓ **የቀድሞው ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች(በአሁኑ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር)** የቢሮ ግንባታ ፕሮጀክት ለተክለብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ ማህበር ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 241,439,140.60 (ሁለት መቶ አርባ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ አርባ ከ60/100 ብር) ውስጥ ብር 170,264,840.31 (አንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺ ስምንት መቶ አርባ ከ31/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የሲቪል አቬንሽ ዋና መ/ቤት የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት** ለቢሃ ኮንስትራክሽን ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 58,513,281.14 (አምሳ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ አስራ ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ አንድ ከ14/100 ብር) ውስጥ ብር 19,067,748.89 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ስልሳ ሰባት ሺ ሰባት መቶ አርባ ስምንት ከ89/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር የግንባታ** ፕሮጀክት ለአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር

224,537,330.43 (ሁለት መቶ ሃያ አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ ሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ከ43/100 ብር) ውስጥ ብር **215,654,040.98** (ሁለት መቶ አስራ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አምሳ አራት ሺ አርባ ከ98/100 ብር) በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ✓ **የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢሮ እና የዲፕሎማቶች** መኖሪያ ግንባታ ፕሮጀክት ለአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 227,098,098.18 (ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ሚሊዮን ዘጠና ስምንት ሺ ዘጠና ስምንት ከ18/100 ብር) ውስጥ ብር **192,833,251.33 (አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ ሁለት መቶ አምሳ አንድ ከ33/100 ብር)** በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ➢ **በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በናሙና ከታዩ 8 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ3** ፕሮጀክቶች ከተከፈለው ብር 299,416,887.77 (ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን አራት መቶ አስራ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ሰባትከ 77/100 ብር) ውስጥ በድምሩ ብር 44,061,442.90 (አርባ አራት ሚሊዮን ስልሳ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ ሁለት ከ90/100 ብር)ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡-
  - ✓ **የዘመናዊ ገራጅ ግንባታ ፕሮጀክት** ለቢሃ ኮንስትራክሽን ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 18,901,036.95 (አስራ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አንድ ሺ ሰላሳ ስድስት ከ95/100 ብር) ውስጥ ብር **9,358,273.14 (ዘጠኝ ሚሊዮን ሶስት መቶ አምሳ ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ከ14/100 ብር)** በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የህይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል** ግንባታ ፕሮጀክት ለአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 275,605,786.39 (ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ከ39/100 ብር) ውስጥ ብር **32,505,401.13 (ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አምስት ሺ አራት መቶ አንድ ከ13/100 ብር)** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **የሐርር ካምፓስ አጥር ግንባታ ግንባታ** ፕሮጀክት ለአዊሀክም ኮንስትራክሽን ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 4,910,064.48 (አራት

ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አስር ሺ ስልሳ አራት ከ48/100 ብር) ውስጥ ብር 2,197,768.63 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ሰባት መቶ ስልሳ ስምንት ከ63/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- **ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በናሙና ከታዩ 5 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ 4** ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር 135,504,085.24 (አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ አራት ሺ ሰማኒያ አምስት ከ24/100 ብር) ውስጥ በድምሩ ብር 60,346,899.69 (ስልሳ ሚሊዮን ሦስት መቶ አርባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ከ69/100) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - ✓ **የአጥር እና ምድረ-ግቢ ግንባታ ፕሮጀክት** ለዳዊት ሀ/ማርያም ኮንስትራክሽን **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 10,929,156.68 (አስር ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ አምሳ ስድስት ከ68/100 ብር) ውስጥ ብር **5,297,547.03 (አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ አምስት መቶ አርባ ሰባት ከ03/100)** በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - ✓ **የተማሪዎች መኖሪያ ጥገና ኮንትራት-2 ፕሮጀክት** ለየትኮንስትራክሽን፣ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን እቃዎች አቅራቢ ጋር ውል **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 4,298,166.11 (አራት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ አንድ መቶ ስልሳ ስድስት ከ11/100 ብር) ውስጥ ብር **2,555,294.29 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አምሳ አምስት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ከ29/100 ብር)** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - ✓ **የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት** ከ3ኤም ኢንጅነሪንግ **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 51,133,402.05 (አምሳ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ሺ አራት መቶ ሁለት ከ05/100 ብር) ውስጥ ብር **505,218.16 (አምስት መቶ አምስት ሺ ሁለት መቶ አስራ ስድስት ከ16/100 ብር)** በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
    - ✓ **የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና መሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት** ለአፍሮፅዮን ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 69,143,360.36 (ስልሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሶስት ሺ ሶስት መቶ ስልሳ ከ36/100 ብር) ውስጥ ብር **51,988,840.21 (አምሳ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺ ስምንት መቶ አርባ ከ21/100 ብር)** በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- **በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በናሙና ከታዩ 4 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ1ፕሮጀክት** (የወንዶገነት ካምፓስ የአጥር ግንባታ ፕሮጀክት) ለስንታየሁ ሥራ ተቋራጭ ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር1,133,720.56 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ሦስት ሺ ሰባት መቶ ሃያ ከ56/100 ብር) ውስጥ በድምሩ ብር 1,003,365.01 (አንድ ሚሊዮን ሦስት ሺ ሶስት መቶ ስልሳ አምስትከ 01/100 ብር) ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡-
- **በወላይታ ዩኒቨርሲቲ በናሙና ከታዩ 7 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ** ለ4ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ ብር **35,174,012.45** (ሰላሳ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ አራት ሺ አስራ ሁለት ከ45/100 ብር) ውስጥ በድምሩ ብር **15,120,315.60** (አስራ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺ ሶስት መቶአስራ አምስት ከ60/100 ብር)ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የአጥር ግንባታ ፕሮጀክት** ለአዱኛ ለማ **የተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 773,191.22 **(ሰባት መቶ ሰባ ሶስት ሺ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ከ22/100 ብር)** በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የመምህራን መዝናኛና ሽንት ቤትና ሻወር ግንባታ ፕሮጀክት** ለማርቆስ መንገሻ ሥራ ተቋራጭ **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 2,044,892.64 (ሁለት ሚሊዮን አርባ አራት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና ሁለት ከ64/100 ብር) ውስጥ ብር**1,760,482.83 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ ሺ አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ከ83/100 ብር)** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **በዳውሮ ታርጫ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ ፕሮጀክት** ለብርሃን ጦቢያው ሥራ ተቋራጭ **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 24,038,059.01 (ሃያ አራት ሚሊዮን ሰላሳ ስምንት ሺ አምሳ ዘጠኝ ከ01/100 ብር) ውስጥ ብር **5,095,344.17 (አምስት ሚሊዮን ዘጠና አምስት ሺ ሶስት መቶ አርባ አራት ከ17/100 ብር)** ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - ✓ **በዋና ግቢ የአመራሮች መኖሪያ ግንባታ ፕሮጀክት** ለጌታቸው አባይ **ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ** ብር 8,317,959.58 (ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ አስራ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ ዘጠኝ ከ58/100 ብር) ውስጥ ብር **7,491,297.38 (ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ዘጠና አንድ ሺ ሁለት መቶ**

ዘጠና ሰባት ከ38/100 ብር) በውሉ መሰረት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 7 ተያይዟል ፡፡

49.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ተቋማችን የቁጥጥር ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ሊያገኝ ይችላል በመሆኑም ውል የተቋረጠበትን አግባብ ከውለታ ሰነዳቸውና ከተያያዥ የህግ ሠነዶች አንፃር በመገምገም አስፈላጊውን ምክረ ሀሳብ ለአሰሪው መ/ቤት ያቀርባል፣በዚህ ሂደት ውስጥ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሳያሳድሱ ወይም ለሚመለከተው የዋስትና ሰጪ ተቋም ሳያሳውቁ የዋስትናው ጊዜ ያለፈባቸው ከሆነ ወደ ክስ በመሄድ በህግ አግባብ እንዲጨርሱ ምክረ ሃሳብ እያቀርብን፣ እንዲሁም በውለታ ጊዜ ውስጥ ያሉ ከሆነ የቅድመክፍያ ዋስትናውን ከሰጠው ተቋም ጋር በመነጋገር የዋስትናውን ገንዘብ እንዲያስመልሱ ለባለቤት መ/ቤት በግብረመልስ እንደሚያሳውቁ ገልጸው ማሳያ ያሏቸውን ማስረጃዎች ለኦዲቱ አቅርበዋል፡፡

50.በሌላ በኩል በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች በክስ ሂደት ላይ የነበሩና በተቋማችን ለቁጥጥር ሥራ ከተመረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያልነበሩ እንዲሁም በፍርድ ቤት ክስ ሂደት ላይ የደረሱ ነበሩ፡፡ ይህንን ስንረዳ በፍርድ ቤት የተያዙ ፕሮጀክቶችን መቆጣጠር ስለማይመለከተን በቁጥጥር ሂደታችን እምብዛም የትኩረት አቅጣጫ አልነበረም፡፡ ስለሆነም በኦዲቱ የታዩ የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን መረጃ በመያዝ ተቋማችን ወደ ሥራ በመግባት የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን የቅድመ ክፍያ አፈፃፀም ያለበትን ሁኔታ አጣርቷል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

- **በፌዴራል መንግስት ህንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት** ባለቤትነት ይከናወኑ የነበሩ እና ውለታቸው ከተቋረጡት 7 ፕሮጀክቶች ውስጥ በ7 ፕሮጀክቶች ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም ገቢ ያልተደረገ መሆኑ የ6 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እስከአሁን የተያዘ ሲሆን ከ7 ውስጥ 1 ፕሮጀክት በመንግሥት ሥራ ተቋራጭ የተያዘ በመሆኑ ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈፃፀም በተመለከተ የመንግሥት ለመንግሥት ድርድር ላይ መሆኑ፣
- **በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር** እየተገነቡ ከነበሩትና ውለታቸው ከተቋረጡት 10 ፕሮጀክቶች ውስጥ 6 ፕሮጀክቶች ባልተመለሰ ቅድመክፍያና ገቢ ባልተደረገ መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እስከአሁን የተያዘ መሆኑ፣

- **በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ተርጫ ካምፓስ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 4 ፕሮጀክቶች ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያና መልካም ሥራ አፈፃፀም ዙሪያ በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እስከአሁን የተያዘ መሆኑና 3 የቅድመ ክፍያ ዕዳቸውን ሙሉ በሙሉ በመክፈላቸው ያልተከሰሱ መሆኑ፣
- **በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ 1 ፕሮጀክት በፍርድ ቤት ክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ ሌሎቹ በተቋማችን በተሰጠ አስተያየት መሠረት ከዋስትና ሰጪ ተቋማት ጋር ድርድር በማድረግ 2 ያልተመለሰ ቅድመ ክፍያ ሙሉ በሙሉ የመለሱበትና ሌሎቹ ወደ ክስ ሂደት ለመሄድ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- **በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ 8 ፕሮጀክቶችን ውስጥ 6 ባልተመለሰ ቅድመክፍያና መልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘ ሲሆን 1 ውለታው እስከ ግንቦት 2014 ዓ.ም ተራዝሞ በውል ውስጥ ያለ መሆኑ 1 ግዴታውን በመወጣቱ ውሉ በስምምነት የተቋረጠ መሆኑ፣
- **በሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ** ይገነቡ የነበሩና ውለታቸው የተቋረጡ 4 ፕሮጀክቶችን ውስጥ ያልተመለሰ ቅድመክፍያ 1 ፕሮጀክት ባልተመለሰ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ ሲሆን 1 ፕሮጀክት ቅድመክፍያ የወሰደውን እንዲመልስ ዋስትናውን ከሰጠው ተቋም ጋር እየተሰራ ይገኛል፡፡ስለሆነም የኦዲት ቡድኑ ይህንን ተረድቶ ከዚህ ጋር በተገናኘ የተያዙ የኦዲት ግኝቶች ሊሰረዙ ይገባል በማለት ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

51.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ ላይ በኦዲቱ የታዩ ከላይ የተዘረዘሩ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ መሆናቸውንና ክትትልም በማድረግ ገንዘቡን ማስመለስ እንደማይቻል የተገለፀ ቢሆንም ከሁለት ፕሮጀክቶች ውጭ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፤ እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውስን ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል በማድረግ ግብረመልስ እየሰጠ ከመቀጠል የዘለለ በደንብ ቁጥር 524/2015 በአንቀፅ5/6 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት እርምጃ እስከመውሰድ የሚያስችል ሥራ በመስራት በሥራ ተቋራጮች ላይ እየታየ ያለውን ቅድመ ክፍያ ወስዶ

ፕሮጀክቶችን ሳይጀምር የመሄድ አዝማሚያ መታረም ያለበት በመሆኑ የተሰሩት ሥራዎች በቂ ናቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡

52.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለፕሮጀክቶች የተከፈለ ቅድመ ክፍያ በወቅቱ ተመላሽ እንዲሆን ባለመደረጉ መንግስት ገንዘቡን ለሌላ የልማት ሥራ እንዳያውለውና ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጓል፡፡

የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርጉ ባለሙያዎች የተመደቡ መሆኑን በተመለከተ

53.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች እና ለሥራ ተቋራጮች ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ እና ተገቢ የሆኑ ባለሙያዎች ስብጥር እንዲሟላ ሊያደርግ ይገባል፡፡

54.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች ቁጥጥር ሥራው ካስቀመጠው መዋቅር አንፃር የሰው ሃይል ማሟላቱ ሲገመገም እስከ 2015ዓ.ም በነበረው መዋቅር 49 በመቶው፤በአዲሱ ደግሞ 65 በመቶ የተሟላ ቢሆንም እንደ ሀገር ከተሰጠው የግልም ሆነ የመንግስት ፕሮጀክቶችን ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ በሰው ሃይል ያልተደራጀ መሆኑ፣
- ❖ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በወሰዱት የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችል የሥራ መደብ በመዋቅሩ ውስጥ ያልተካተተ እና ለስራውም የተመደበ የሰው ኃይል የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

55.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን መጀመሪያ ሲቋቋም ባለው ክፍት የስራ መደቦች ላይ በተለያየ መንገድ የሰው ሀይል ማሟላት የሚቻል የነበረ ሲሆን ከ2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ግን ቅጥርና ደረጃ ዕድገት በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ምንም ዓይነት ቅጥርና ዝውውር እንዳይፈፀም ተከልክሏል፡፡

56.ተቋሙ በ2015 በጀት ዓመት አዲስ ባስጠናው አደረጃጀት መሠረት 361 የስራ መደቦች ያሉት ቢሆንም የሰራተኛ ድልድል ተሰርቶ የሰው ሀይል ሽፋን 53% ብቻ ሲሆን ይህ ለተቋሙ ከተሰጠው ተልዕኮና ኃላፊነት አንፃር ሲታይ በተለይ በዓላማ

ፈፃሚ የስራ ክፍሎች ላይ ከፍተኛ የሰው ሀይል እጥረት የሚታይና አንድ የስራ ክፍል ውስጥ ዴስክ ብቻ ያለበት በመሆኑ ተቋሙ እንደ ሀገር ይዞ የተነሳውን ራዕይና ተልዕኮውን ከግብ ለማድረስ እና ዋና ዋና ዕቅዶቹን ለማሳካት ከፍተኛ ተግዳሮት የፈጠረ ስለሆነ ያለው የስራ ክብደትና እንደ ሀገር የተሰጠውን ኃላፊነት በጥልቀት ታይቶ በልዩ ሁኔታ ቅጥር እና ዝውውር ካለው የስራ መደብ እና በጀት አንፃር ተገምግሞ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመወያየት እንዲፈቀድላቸው በተደጋጋሚ እያሳሰቡ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

57.የባለስልጣን መ/ቤቱ ሃላፊዎች ይህን ቢሉም ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በወሰዱት የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችል የሥራ መደብ በመዋቅሩ ውስጥ ያልተካተተበትን እና የሰው ኃይል ያልተመደበበትን ምክንያት ምላሽ ያልተሰጠ ከመሆኑም በተጨማሪ የመ/ቤቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የቅጥር ይፈቀድልኝ ጥያቄ ለሚመለከተው አካል ስለማቅረቡ እና እንደ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በተለየ መልኩ የሰው ሃይል እንዲያሟላ ተደጋጋሚ ጥረት ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡

58.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባስቀመጠው መዋቅር እስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎችን አሟልቶ እና በመዋቅሩ ያልተካተቱ መደቦችን አካቶ አለመስራቱ የክትትልና ቁጥጥር ስራውን በተሰጠው ኃላፊነት ልክ እንዳይወጣ አድርጓል፡፡

ለተቋረጡ የመንግስት ፕሮጀክቶች ቁጥጥር እና ለሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ ለማሻሻል ጥናቶች መካሄዳቸውን በተመለከተ

59.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች ቁጥጥር እና ለሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ እና ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችን በማስጠናትና በጥናቱ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡

60.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ወደ አስር የሚሆኑ ጥናቶችን ብር 17,789,840.81 (አስራ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ አርባ ከ81/100 ብር) ወጪ አድርጎ ያስጠና ቢሆንም በኦዲት አካባቢው ዙሪያ በተጠኑ

ጥናቶች መሻሻል የሚገባቸው ተብለው ከተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ውስጥ ተግባራዊ ያልተደረጉ መኖራቸው፤

❖ ለማሳያ ያህል፡-

- ✓ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባጠናው የኮንስትራክሽን ሱፐርቪዥን በኢትዮጵያ ያለውን ህጋዊ ክፍተት በዳሰሰበት ጥናት ላይ አማካሪዎች እንደሥራ ተቋራጮች እኩል ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸውና አማካሪዎች የመልካም ሥራዋስትና (Performance Guarantees) መጠየቅ እንዳለበቸው፤ ለፕሮጀክቶች ጥራት ቁጥጥርና ደህንነት ወጥ የሆነ ማንዋል መዘጋጀት እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባጠናው በኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ፈቃድ አሰጣጥ ያለውን ህጋዊ ክፍተት በዳሰሰበት ጥናት ለሥራ ተቋራጮችም ሆነ ለአማካሪዎች አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ፣ ደረጃ ሲያድጉ እና እድሳት ሲያደርጉ ከመመሪያው ከተቀመጠው መስፈርት በተጨማሪ በየፕሮጀክቶቻቸው የሚያሰማሩቸው ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃት (professional Competency)፤ አጠቃላይ የፕሮጀክት አፈፃጸማቸው (በጥራት፣ በውል መሰረት በተመደበው ዋጋ እና ጊዜ ማጠናቀቅ እና የፕሮጀክት ማኔጅመንት ብቃት) በመገምገሚያ መስፈርትነት ተቀርፀው ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው፣ የማሽነሪዎች ብቃት (Machinery performance) ማረጋገጫ እንደ አንድ መስፈርት መቀመጥ እንዳለበት እንዲሁም ከፌዴራል እስከ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ያለው የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሥርዓት ተመሳሳይ በሆነ ህግና ሥርዓት መመራት እንዳለበት የተቀመጠ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤ ታይቷል፡፡

61. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ያስጠናቸውን ሁሉም ጥናቶች ወደ ተግባር ያስገባ ሲሆን የጥናቱ መነሻ ተቋሙ ወደ ሥራ ከገባ በኋላ የኢንዱስትሪውን የሬጉላቶሪ ሥራዎች ለመስራት ትልቁ ተግዳሮት ሆኖ ያገኘው የኢንዱስትሪውን የአፈጻጸም ደረጃዎች ሊያሳዩ የሚችሉ መረጃዎች እጥረት እና ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ የአሰራር ስርዓቶች አልነበሩም፡፡ በመሆኑም ተወዳዳሪ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት የተቀመጠውን ርዕይ ለማሳካት የተጣሉ ስትራቴጂያዊ ግቦችን አፈጻጸም ትርጉም ባለው ሁኔታ

ለመከታተል እና ለመገምገም ያስችል ዘንድ 8 ጥናቶች የመነሻ ሁኔታዎችን (Baseline) በዋናነት ለማወቅ ሲሆን ይህን ለስትራቴጂ ተጠቅመንበታል፡፡

62.እንዲሁም የኢንዱስትሪውን የአፈጻጸም ክፍተቶችን ለመለየት በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት የተጠናው ጥናት ባስቀመጠው ምክረ-ሀሳብ መሠረት በከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ተነሳሽነት የኮንስትራክሽን አማካሪ ድርጅቶችን ተጠያቂነት በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ሌላው ከፌዴራል እስከ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ያለው የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሥርዓት ተመሳሳይ ህግና ሥርዓት ተፈጻሚ እንዲሆን ከማድረግ ረገድ ሁሉም ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች በፌደራል ደረጃ የወጣውን መመሪያ የሚተገብሩ ሲሆን በአንዳንድ የክልል መስተዳደሮች እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በሚል የተወሰኑ ሁኔታዎችን በመጨመር በመመሪያቸው ላይ አካተው በሥራ ላይ እንዲውል እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በአፈጻጸሙም ዙሪያ በተለያዩ ጊዜ የቴክኒክ ድጋፎችን እንዲያገኙ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

63.በረቂቅ ሪፖርት ምላሽ በዋናነት ጥናቶቹን ማስጠናት አስገዳጅ የሆነበት ምክንያት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ወቅት መነሻ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ ጠቋሚ መረጃዎች ባለመኖራቸው የዕቅዱን ተፈጻሚነት በተለይ በአለም አቀፍ መመዘኛዎች ለመመዘን ታስቦ (ከየት ተነስቶ የት ደረሰ) የሚለውን ጉዳይ ለመፍታ እና ጥናት ላይ የተመረኮዙ ምክረ-ሀሳቦችን በማግኘት እንደየሁኔታው በስራ ላይ ለማዋል ታስቦ ነው፡፡ በመሆኑም የኮንስትራክሽን አማካሪ ድርጅቶችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ወይም ለማስፈጸም የህግ ማዕቀፍ ሊዘጋጅለት እንደሚገባ የተሰጠውን ምክረ-ሀሳብ ተከትሎ የተዘጋጀውን መመሪያ (መመሪያ 881/2014) ሶፍት ኮፒ ስካን የተደረገ ሰነድ ተያይዞ መቅረቡን ገልፀዋል፡፡

64.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ጥናት መጠናቱ እና የጥናቱን ውጤት ለመተግበር የሚደረገውን ጥረት በጥሩ ጎኑ የምንመለከተው ሲሆን፣ በተሰራው የኦዲት አካባቢ ዙሪያ የተጠኑና ለባለሥልጣኑ ስራ መሻሻል ጠቃሚ የሆኑ ከላይ በማሳያነት የቀረቡትን ጨምሮ ሌሎች በጥናቶቹ የተካተቱ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ያልተደረጉ መኖራቸውና አሁንም ድረስ ችግሮች ያሉ መሆኑ፣ እንዲሁም የአማካሪ ድርጅቶችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀ መመሪያ 881/2014ን ጨምሮ ሌሎች ቀርበዋል እና ተሰርተዋል ተብለው የተጠቀሱ ተግባራት ማስረጃዎች ያልቀረቡ በመሆኑ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

65.በመሆኑም የተጠኑ ጥናቶች በተጠኑበት አላማ መሰረት ወደ ተግባር እንዲገቡ አለመደረጉ በጥናቶቹ መሻሻል አለባቸው ተብለው የተቀመጡ ችግሮች ወቅቱን የጠበቀ መፍትሔ እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

II. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ህጎች መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት አጠባበቅ በተመለከተ

66.ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ሊዘረጋና አፈፃፀማቸውንም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

67.ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገ የአካል ምልከታና ቃለ መጠይቅ በናሙና በታዩ ግንባታ ላይ ባሉ 7 ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን ክፍተቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

- ✓ የሰራተኞች የስራ ልብስ፣ የጭንቅላት መከላከያ ቆብ፣ የሥራ ጫማ ስቶር ውስጥ ከማስቀመጥ ውጭ ጥቅም ላይ እያዋሉ አለመሆናቸው፤
- ✓ የተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ሰራተኛው ወይም ማህበረሰቡ እንዳይገባ መከለያ አጥሮች የማይደረጉ መሆናቸው፤
- ✓ በግንባታ ወቅት ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ በሚችሉባቸው ቦታዎች የመቅለቢያ መድረኮች ያልተዘጋጁ መሆናቸው፤
- ✓ ከአምስት በላይ ፎቅ ያላቸው የህንፃ ፕሮጀክቶች የሚጠቀሙበት መወጣጫ ብረት መሆን ሲገባው እንጨት እየተጠቀሙ መሆኑ፤
- ✓ በሥራ ቦታዎች ለሠራተኞች እንቅስቃሴ አስፈላጊ ከሆኑ ቦታዎች ውጭ ያሉ ክፍተቶች ተሸፍነው ለሠራተኛው አደጋ መቀንስ በሚችል መልኩ ያልተዘጋጁ መሆኑ፤
- ✓ የህንፃዎች ውጫዊ ክፍል የማይሸፈን መሆኑ፤
- ✓ የመጀመሪያ እርዳታ ሊሰጥ የሚችል ጊዜያዊ ክሊኒክ /ባለሙያ የሌለ መሆኑ፤ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

68.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ፣በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ተቋማችን ከላይ በተገለፁት የአከባቢና የማህበረሰብ እንዲሁም የግንባታ ተጠቃሚዎች እና በሚገነባው ግንባታ ላይ የደህንነትና የጤንነት ማስጠበቅ ሥራን እንደዋነኛ ተግባር በማድረግ እየሰራ ይገኛል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ደህንነትና ጤንነትን በሚመለከት አሁናዊ ሁኔታና ወደፊት መተግበር ያለባቸው አሰራሮች በሚል በጅማ ዩኒቨርሲቲ ጥናት አስጠንቶ ወደ ትግበራ እየገባን እንገኛለን፡፡ ከደህንነትና ጤንነት ጋር በተያያዘ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚፈጠረውን ችግር በየጊዜው በግንባታ ቁጥጥር እያነጠረ ቢያወጣም እርምጃ ለመውሰድ እንደተባለው የህግ ማዕቀፍ ክፍተት ስለነበረ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አዋጅ ረቂቅ ሰነድ አዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረቡ መዘንጋት የለበትም፡፡ በተጨማሪም ባለስልጣኑ ከደህንነትና ጤንነት አንፃር ወደ ግንባታ ሊገቡ የሚመጡ ዲዛይኖችን በመቆጣጠር አስፈላጊውን እርምት በዲዛይኖች ላይ እየወሰደ መቆየቱ፣ እንዲሁም በክልልና በከተሞች የሚገነቡ ግንባታዎች ይህንን ተግባር እንዲያከናውኑ የህጎችና ስታንዳርዶች አተገባበር ቁጥጥር እየተደረገ ግብረመልስ እየተሰጠ መቆየቱን ገልፀዋል፡፡

69.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ እየፈጠሩ ባሉት ጉዳት ልክ ባለስልጣኑ የቁጥጥርና የክትትል ድርሻውን ያልተወጣ እና አሁንም በኦዲቱ ወቅት ችግሮቹ መኖራቸው የተረጋገጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያቸግራል፡፡

70.የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ እያደረሱ ያሉትን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል ሥራ ባለመሰራቱ በሰራተኛች እና በህብረተሰቡ ላይ የሞት፣የአካል ጉዳት እና ከፍተኛ የንብረት ውድመት እንዲደርስ አድርጓል፡፡

በኮንስትራክሽን ስራዎች ላይ የሚፈጠሩ የአደጋ አጋጣሚዎችን መረጃ አያያዝንና ክትትል በተመለከተ

71.ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተመለከተ ስለመካተቱ ሊያረጋግጥ እና በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎ ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊፈትሽ ቁጥጥርና ክትትልና ሪፖርት በማድረግ የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

72.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን ከሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች ውጪ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን አካተው ተግባራዊ እያደረጉ ስለመሆኑ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑ፤
- ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ ባለመያዙ ናሙናዎችን መርጦ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤
- በ2014 ዕቅድ አፈፃፀም 1804 እና በ2015 የ9 ወር ዕቅድ አፈፀም ላይ 142 በአጠቃላይ 1946 የአደጋዎች መረጃ እንደተሰበሰበ የተቀመጠ ቢሆንም መረጃው በቁጥር ብቻ የተቀመጠ እንጂ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ ደረሰ የሚለውን ከትክክለኛ የመረጃው ምንጭ ያልተገኘ መሆኑ እና በደረሱ አደጋዎች ላይ በህግ መሰረት ተጠያቂነት እንዲኖር ስለመደረጉ የተሰራ የክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

73.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ እንደ ሀገር በመንግስትም ሆነ በግል ኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ መረጃ እና በየትኛው ቦታ ምን አይነት መረጃ፣ የት እንደተከሰተ፣ ምን አይነት አደጋ እንደሆነ እንዲሁም በየትኛው ክልልና ከተማ እንደተከሰተ መረጃው ተደራጅቶ ቢገኝም የቁጥጥር ሥራ በተደረጉት ፕሮጀክቶች ግን በሚፈለገው ደረጃ ያለማደራጀት እና እርምጃ በመውሰድ ዙሪያ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

74. እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011 ተሰጥቶት የነበረው ሥልጣንና ተግባር የፌዴራል መንግሥት ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ እንድናተኩር ያደረገ ሲሆን ከደንብ ቁጥር 524/2015 በኋላ ይህንን ሥራ ለማከናወን በተቋሙ

አዲስ አደረጃጀት ዘርግቶ የኮንስትራክሽን ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዘርፍ ይህንን ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ የሚያስፈፅም ይሆናል፡፡

75.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ አደጋዎች መረጃ በተደጋጋሚ በተጠየቀበት ወቅት ከፌደራል ፖሊስ፤ ከእሳት እና ድንገተኛ አደጋዎች…ወዘተ የተሰበሰቡ እና ምን ያህል የሞትና የንብረት አደጋ መሆናቸውን በቁጥር ብቻ የሚገልፁ መረጃዎች የቀርበ ሲሆን እንደተቆጣጣሪ መ/ቤት ቀጥታ አደጋው ከተከሰተባቸው የኮንስትራክሽን ዘርፎች በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚገልፅ በባለስልጣኑ ተመዝግቦ የተያዘ የተደራጀ መረጃ ያልተገኘ በመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ናሙናዎችን ወስዶ በመስራት እየደረሰ ያለውን የጉዳት መጠን በማረጋገጥ መተንተን እንዳልተቻለበት ሁኔታ በመፈጠሩ የተደራጀ መረጃ አለ የሚለውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

76.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ አደጋዎችን መረጃ አደራጅቶ በመያዝና በመፈተሽ ክትትል አለማድረጉ በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች እየደረሱ ባሉ አደጋዎች ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች ፍትህ እንዳያገኙና ተጠያቂነት እንዳይኖር ከማድረጉ በተጨማሪ በሀገር ደረጃ የጠፋው ጥፋት እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

III. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ በህግ መሰረት መከናወኑን እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፤

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማስተዳደር የወጡ ህጎችና ደንቦችን መተግበራቸውን በተመለከተ

77.በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮችን ፈቃድ አሰጣጥ እና የፕሮጀክቶችን ቁጥጥርና ክትትል የሚመለከቱ አዋጆች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

78.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው የመቆጣጠር ሥልጣን መሰረት ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ ግብረ መልስ የተሰጣቸው የፕሮጀክት ባለቤቶች በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ማስተካከያ ሳያደርጉ ሲቀሩ

እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክት ቁጥጥርና አፈፃፀም መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፤

- ❖ ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለየትኛው ጥፋት ምን አይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በግልፅ የሚያስቀምጥ የክትትልና ቁጥጥር መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- ❖ በፌዴራል እና በክልል ያሉ የመንግስትም ሆነ የግል ፕሮጀክቶች የትኞቹ ፕሮጀክቶች በፌዴራል ደረጃ የትኞቹ ደግሞ በክልል ደረጃ መመዝገብ እንዳለባቸው በግልፅ የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ ያልተዘጋጀ በመሆኑ ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ፕሮጀክቶችን መዝግበው እንዳይዙ እንቅፋት የፈጠረ መሆኑ፤
- ❖ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አዋጅ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል አፀድቆ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ❖ በመመሪያ ቁጥር 648/2013 ለብቃት ማረጋገጫ አሰጣጡ እንደተግዳሮት ይነሱ የነበሩ ነጥቦችን ለማሻሻል ረቂቅ የመመሪያ ማሻሻያ ያዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል አፀድቆ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ❖ መሻሻል ያስፈልጋቸውል ከተባሉት መሃከል ለማሳያ ያህል፡-
    - ✓ ባለሙያ ላልሆነ የድርጅት ባለቤት ቴክኒካል ስራአስኪያጅ ለሚያደረግዉ የፕራክሲንግ ባለሙያ ለቀጠረ 20% የባለቤትነት ድርሻ እንዲሰጥ የተቀመጠዉ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈለገ በመሆኑ፤
    - ✓ የፕራክሲንግ ባለሙያ ቅጥር ከደረጃ 2 እከ 7 የነበረዉ ለደረጃ 1 ጀምሮ 6 እንዲሆን ያስፈለገ በመሆኑ፤
    - ✓ በልዩ ሁኔታ የተቋራጭነት ፈቃድ አሰጣጥ ልምድ አያያዝ መሻሻል ያስፈለገ በመሆኑ፤
    - ✓ በዉሃ ፣ በህንጻና በመንገድ ተቋራጭነት ሲሰጡ የነበሩ ተመሳሳይነት ስራዎች ያላቸዉን ወጥ ማድረግ ያስፈለገ በመሆኑ፤
    - ✓ በገንዘብ ይጠየቅ የነበረዉ የመሳሪያ ኪራይ ማሻሻል ያስፈለገ በመሆኑ፤
    - ✓ ለደረጃ 7 ይጠየቅ ነበረዉ የፕራክትሲንግ ባለሙያ ማሻሻያ ያስፈለገ በመሆኑ የሚሉት እና ሌሎችም ችግሮች መሻሻል እንደሚገባቸው የተለዩ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ፀድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

79.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ እርምጃ ለመውሰድ የህግ ማዕቀፍ ክፍተት ስለነበረ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አዋጅ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርበናል፡፡ ይሁን እንጂ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሃሳብ በማመንጨት ለአዋጅና መመሪያ አውጭ አካል ከመስጠት ውጭ አዋጅም ሆነ መመሪያ የማዘጋጀት ተግባርና ሃላፊነት ባይኖረውም ፕሮጀክት ምዝገባን በተመለከተ ሃሳብ በማመንጨት የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ 648/2013 እንዲዘጋጅ በተደረገው መመሪያ ክፍል ሰባት ላይ የፕሮጀክት ምዝገባ የተቀመጠ ሲሆን በአንቀፅ 33/7 ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ፕሮጀክቶችን እንደሚመዘገብ ያስቀምጣል፡፡ በዚሁ መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ የፌዴራል ፕሮጀክቶችን ከክልሎችም ጋር በመቀናጀት እየመዘገቡ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

80.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አዋጅ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረቡ የተገለፀ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ፀድቆ ተግባራዊ በመሆኑ፣ በመመሪያ 648/2013 ፕሮጀክት ምዝገባን በተመለከተ የተቀመጠው አንቀፅ የፌዴራሉን እና የክልሎችን ድርሻን በግልፅ ያስቀመጠ ባለመሆኑ እና በክልሎች በአካል ተገኝተን ቃለ መጠይቆችን ባደረግን ወቅት መመሪያው ግልፅ ባለመሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመመዝገብ በመቸገራቸው የገለፁና እስካሁንም የፕሮጀክት ምዝገባ ያልጀመሩ መኖራቸውን የተረጋገጠ በመሆኑ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ፕሮጀክቶችን እየመዘገብን እንገኛለን የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

81.በመሆም የፕሮጀክት ባለቤቶችን፣ ሥራ ተቋራጮችን እና የክልሎችን ሚና ለይተው የሚያስቀመጡ መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ አለመሆናቸው ሁሉም አካላት በተገቢው ሁኔታ ኃላፊነታቸውን እንደይወጡ ከማድረጉም በተጨማሪ ህገ ወጥ በሆኑ ተግባራት ተሰማርተው ሲገኙ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

ለሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ

82.ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ፣ የህንፃ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (ማሽነሪ፣ አመታዊ ተርንአቨርና የሰው ኃይል…) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

83.በኦዲቱ ወቅት በናሙና የተመረጡ በቀድሞው መመሪያ ቁጥር 19/2006 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 40 እና በአሁኑ መመሪያ ቁጥር 648/13 መሰረት

የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ 40 በአጠቃላይ 80 የሥራ ተቋራጮች የግል ማህደር ሲከለስ የሚከተሉት ታይተዋል ፡፡

- ❖ በየደረጃው የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን ሳያሟላ የደረጃ-3 የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው አንድ ሥራ ተቋራጭ መኖሩ፤
- ❖ የማሽነሪ ቴክኒካል ምርመራ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና ሳያድሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲያድጉ የተደረጉ 2 ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤
- ❖ በናሙና የታዩ ሁሉም ሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ በሰው ኃይል መስፈርትነት የሚያቀርቧቸው ባለሙያዎች እና በልዩ ሁኔታ የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ባለሙያዎች የሚያቅርቡት የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ መጠየቅ ያለበት ቢሆንም በመመሪያው በመስፈርትነት ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- ❖ በመመሪያ 648/13 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸው በናሙና ከታዩ 40 ሥራ ተቋራጮች ውስጥ አንድ ሥራ ተቋራጭ ለሰው ኃይል መስፈርትነት ያቀረበው ባለሙያ የትምህርት ማስረጃው እና የሙያ ምዝገባ ሰርተፊኬቱ በተለያየ ሰው ሆኖ እንደ አንድ ሰው ማስረጃ የቀረበና ተቀባይነትን ያገኘ መሆኑ ፤
- ❖ በማህበር ተደራጅተው የደረጃ አምስት ሥራ ተቋራጭነት ሲወስዱ የማህበሩ አባል ያልሆነን ሰው መታወቂያ አስይዘው የብቃት ማረጋገጫውን የወሰዱ መሆኑ፤
- ❖ በተለያዩ ደረጃዎች በልዩ ሁኔታ በብቃት አሰጣጥ መመሪያው አንቀፅ 27 መሰረት ከተሰጣቸው ባለሙያዎች ውስጥ አንድ ባለሙያ የተሰጠውን ደረጃ-5 ሊያሰጥ የሚያስችል በራሱ ወይም በተቆጣጣሪነት የሰራውን ሥራ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፤
- ❖ በየደረጃው የተቀመጠውን የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በመስፈርቱ መሰረት ሳያሟላ በብዛት ያለውን ብቻ በማቅረብ፣ ማሽንን በተሽከርካሪ በማተካካት ከሚያዚያ 2013 ዓ.ም በኋላ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሥራ ተቋራጭ መኖሩ፤
- ❖ ከሚያዚያ 2013 ዓ.ም በኋላ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የደረጃ ማሻሻያ ያደረጉ ተርን ኦቨር ማቅረብ የነበረባቸው 4 ሥራ ተቋራጮች የድርጅቱን

ተርን ኦቨር የሚያሳይ በውጭ ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤

- በናሙና ለታዩ 10 ልዩ ስራ ተቋራጮች የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ዘርፍ እና መመሪያ ላይ የተቀመጠው ዘርፍ ባለመመሳሰሉ የተሰጡትን የብቃት ማረጋገጫዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰርት ለመገምገም ያልተቻለ መሆኑ፤ለማወቅ ተችሏል፡፡

84.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በመመሪያ ቁጥር 19 ላይ በሰንጠረዥ 6፣ 7 እና 8 ላይ በተቀመጠው የእፎይታ ጊዜ በሁለት አመት ውስጥ ማሟላት የሚጠበቅበትን ዝቅተኛውን መስፈርት እንዲያሟላ ይፈቅዳል፡፡ በሌላ በኩል በልዩ ሁኔታ በመመሪያ 19/2006 እና መመሪያ 648/2013 በሚመዘገቡበት ወቅት ምንም ዓይነት የተሽከሪካሪም ሆነ ተጨማሪ የሰው ሃይል እንዲያሟሉ ስለማይጠይቅ እነዚህን ሁኔታዎች መሰረት አድርጎ የተሰጠ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

85.በመቀጠልም የቴክኒክ ምርመራን በተመለከተ ደግሞ የዕድሳት ዘመኑን (የቴክኒክ ምርመራ ስለመደረጉ እና ስላለመደረጉ) በሁለት መንገድ እንደሚረጋገጥ ይህውም ተገልጋይ የታደሰ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ሊብሬ ሲያቀርብ ወይም በዋስትና ወይም በዕገዳ ምክንያት የባለቤትነት ማረጋገጫው ወይም ሊብሬው ሲያዝ ባለቤቱ ማሳደሱን የምናረጋግጠው በእጁ በሚሰጠው ሰነድ መሆኑን፣ በሰው ኃይል መስፈርትነት የሚቀርቡ ባለሙያዎች የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ መመሪያዉ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ባለሙያዎች የሚያቀርቡት የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ ይጠየቃል። ማስረጃው እና የሙያ ምዝገባ ሰርተፊኬቱ በተለያየ ሰው ሆኖ እንደ አንድ ሰው ማስረጃ የቀረበ መኖሩ የሚለው ግኝቱ ትክክል ነው:: ይህ ችግር ሊፈጠር የቻለበት ምክንያት ሪቪው በሚደረግበት ወቅት የተደረገ ስህተት ነው:: ነገር ግን ስለባለሙያው ጠለቅ ብለን ባደረግነው ማጣራት በባለሙያ ምዝገባ ወቅት በትክክል የትምህርት ማስረጃውን አያይዞ የተመዘገበ ቢሆንም ቀጣሪው ድርጅት ለዕድሳት ምዝገባ በሚያመለክትበት ወቅት ሌሎች ዶክመንቶችን (የሙያ ፍቃድ፣ የስራ ልምድ እና የቅጥር ውል) በትክክል ተያይዘው የትምህርት ማስረጃው ግን የሌላ ባለሙያ አያይዞ የተገኘ በመሆኑ፤ የማህበሩ አባል ያልሆነን ሰው መታወቂያ አስይዘው የወሰዱ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ ከማህበሩ አባላት ውጪ ህጋዊ ውክልና የተሰጠው ግለሰብ ማንነት የሚገልፅ መታወቂያ ሲሆን ሌላኛው በ E-service አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በስህተት

የሌላን ሰው መረጃ የሚደባለቅበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ በዚህን ግዜ ተገልጋዩን ላለማስቸገር በማመልከቻው ላይ ምንም ችግር እንደማይፈጥር ሲታወቅ ሂደቱ እንዲቀጥል የሚደረግበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡

86.እንዲሁም በመመሪያ 648/2013 አንቀፅ 40 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ መሰረት መመሪያ 19/2006ን በምንጠቀምበት ወቅት የማሽነሪዎች፣ ተሸከርካሪዎች እና ባለሙያዎችን መተካካት በሚፈቅደው የመመሪው ክፍል ሰንጠረዥ 4 እና 5 መሰረት የተፈጸመ መሆኑ፤ተርን ኦቨርን በተመለከተ ከገቢዎች ፅ/ቤት በሚያቀርቡት ያለፉትን አምስት ዓመታት ከፍተኛ የሽያጭ መጠናቸው የሚገልፅ ማስረጃ አቅርበው በዚህ አግባብ የተስተናገዱ ሊኖሩ የሚችሉ በመሆኑ፤ልዩ ስራ ተቋራጮችን በተመለከተ በአዲሱ የንግድ መደቦች አወጣጥ ላይ መደቦች ጠቅለል ተደርገው በስራቸው ሌሎች ንዑስ ዘርፎችን በያዘ መልኩ በመኖሩ አገልግሎት ጠያቂው ዋናውን መደብ ስያሜ በአገልግሎት መጠየቂያው ላይ በሚሞላበት ወቅት ከንዑስ ዘርፎች ውስጥ በሚመጥነው ወይንም በሚያሟላው ዘርፍ የሚመዘገብ ይሆናል ለምሳሌ:- የግንባታ ማጠናቀቅ ስራ ተቋራጭ የሚለው መደብ ስር አስር ዘርፎች አሉ በማለት መመሪያ 648/2013 ዕዝል 5 ስር መመልከት እንደሚቻል፤መመሪያ 648/2013 በማይፈቅደው ደረጃ የተሰጠ መሆኑን በሚመለከት ደግሞ በመመሪያ 648/2013 በልዩ ስራ ተቋራጮች ስር በደረጃ ስምንት የሚመዘገቡ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

87.በረቂቅ ሪፖርት በተሰጠ ምላሽ በየደረጃው የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በተመለከተ ሳያሟሉ የወሰዱ ተቋራጮች የሉንም። እናም በደረጃ -4 የወሰደው አንደኛው ተቋራጭ በመመሪያ ቁጥራችን 648/13 መሰረት ሲሆን በሶስት(3) ተመጋጋቢ ፕራክቲሲንግ በልዩ ሁኔታ ተደራጅተው የሚወስዱት የፈቃድ አይነት ነው።ሁለተኛው ተቋራጭ ደግሞ በወቅቱ ባልታደሰ መታወቂያ ቀርቦ የተስተናገደበት ምክንያት በወቅቱ በሀገራችን በነበረው ጊዜያዊ መታወቂያ እድሳት ክልከላ ምክንያት ሲሆን ይህም ተቋራጩ በዛን ወቅት ብቃት ያወጣ ከመሆኑ ጋር የሚያያዝ ሁነት ነው። ሶስተኛውን ተቋራጭ በተመለከተ በኢ- ሰርቪሱ ፕሮግራም ላይ የቦታ መዘበረረቅ ችግሮች ሲኖሩበት ይህም ከኢ-ሰርቪሱ ዌብሳይት ዳታ አቀባበል የመልማት ችግር ጋር የሚገናኝ እየተስተካከለ ያለ ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

88.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የጎደሉም ሆነ ያላግባብ የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች፤መታወቂያ፣ የኢ-ሰርቪስ የዳታ መዘበራረቅ፣ ተርን ኦቨር እና ሌሎችም ግኝቶች መመሪያው ካስቀመጣቸው ልዩ ሁኔታዎች እና በመደበኛ

መስፈርትነት ከተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች አንፃር ታይተውና ተገምግመው ባለሥልጣኑ ለወደፊት ለሚሰራው ሥራ ሊማርባቸውና ሊታረምባቸው ይገባል ተብለው በትክክለኛ ማስረጃ ላይ ተመስርተው የተቀመጡ ነጥቦች መሆናቸውን የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በተላከ ወቅት ከሥራ ክፍሉ ሠራተኞች ጋር ተማምነን ወደ ሪፖርት እንዲገቡ የተደረጉ እንጂ ከላይ በተሰጠው ምላሽ አግባብ መመሪያው ያስቀመጣቸውን ልዩ ሁኔታዎች እና አማራጮች ካለመረዳት የተቀመጡ ግኝቶች ባለመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

89.በመሆኑም በየደረጃው ያሉ ሥራ ተቋራጮች በኮንስትራክሽን ዘርፉ ለመሰማራት የሚያበቃቸውን በደንብና መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶች ሳያሟሉ፣የሚቀረቡ አስፈላጊ ሰነዶች በአግባቡ ሳይረጋገጡ የብቃት ማረጋገጫው መሰጠቱ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጡን በተመለከተ የወጡ ህግና ደንቦች እንዳይከበሩ ከማድረጉም በተጨማሪ ለአገልግሎት ጥራት ችግር፣ለብልሹ አሰራር (ሙስና) እና የመልካም አስተዳደር ላይ ችግር በመፍጠር ለሁሉም ዜጋ እኩል አገልግሎት መስጠት እንዳይቻል በማድረግ የቅሬታ ምንጭ እንዲሆን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ለውጭ አገር ሥራተቋራጮች የሚደረገውን ቁጥጥርና ክትትል በተመለከተ

90.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጭነት (ጠቅላላ፣ የህንፃ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) ለሚሳተፉ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

91.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች እንዳሉ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ከ14 ሥራ ተቋራጮች ውጪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በምዝገባ መመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፤
- ❖ በመመሪያ ቁጥር 648/13 መሰረት በደረጃ አንድ ሥራ ተቋራጭነት (በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ) የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው 10

የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች የግል ማህደር ተወስዶ ከታዩ ሥራ ተቋራጮች ውስጥ ለደረጃ አንድ የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሳያሟሉ እና በማሽን ቦታ ተሽከርካሪ በማተካካት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው 3 ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤

- የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ በሰው ኃይል መስፈርትነት የሚቀርቡ ባለሙያዎች የሚያቀርቡት የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ የማይጠየቅ መሆኑ፤በመስፈርቱ የተቀመጠውን ተርን ኦቨር ሳያሟሉ እና የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ያጠናቀቁ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፣ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው፤ የሚሉ ናቸው፡፡

92.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ የውጭ ስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ምዝገባው ይካሄድ የነበረው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የነበረ ሲሆን ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የብቃት ማረጋገጫ ምዝገባው ወደ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ከመጣ በኃላ እድሳት ፈልገው ለሚመጡት የውጭ ስራ ተቋራጮች አገልግሎት እየሰጠን ሲሆን፤ ቁጥጥሩን በተመለከተ በዚህ በጀት ዓመት ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመሆን ትኩረት አድርገው እየሰሩ እንደሚገኙ የገለፁ ሲሆን ቀደም ብለው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተመዝግበው የነበሩ የውጭ ሀገር ስራ ተቋራጮች በተመለከተ በሀገራችን ውስጥ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ነባር ስራ ተቋራጮች ለተቋማችን እንጂ ለሀገሪቷ አዲስ ባለመሆናቸው ምክንያት በመመሪያ 648/2013 አንቀፅ 40 የሽግግር ድንጋጌን ለነዚህም የሚመለከት ሲሆን በዚህም መሰረት በማድረግ የዕድሳት አገልግሎት በቀድሞ መመሪያ ቁጥር19/2006 ሲመዘገቡ የነበረ ሲሆን እንዲሁም የሀገራችንን ገፅታ እና ዲፕሎማሲያችንን በሚያስጠብቅ መልኩ ህጋዊ የምዝገባ አገልግሎት ለመስጠት ሲባል በቀጥታ በአዲሱ መመሪያ 648/2013 እንዲገቡ ባለመደረጉ በቀድሞ መመሪያ ላይ ከላይ የተጠቀሱትን መተካካትን እና እፎይታ ጊዜን በመጠቀማቸው ምክንያት ነው፡፡ ያልተሟሉ ሰነዶችን በተመለከተ በቀድሞ መመሪያ ቁጥር19/2006 የመሸጋገሪያ የጊዜ ገደቡ ባለማለቁ እየተመዘገቡ በመሆኑ ነው፡፡ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ ባለስልጣኑ የሰራው በመጀመርያ መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተሰርታል፡፡ እንዲሁም ሁሉም ኮንትራክተሮችና ባለሙያዎች ወደ

መስሪያ ቤታችን መጥተው እንዲመዘገቡ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና በሌሎች ሚዲያዎች በተደጋጋሚ የማስታወቅያ ሥራ ተሰርታል በማለት አብራርተዋል፡፡

93.የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የውሃ ዘርፍን ሳይጨምር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች ውስጥ 12 ሥራ ተቋራጮች ከ2013 በኋላ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው በመሆኑ፣ እድሳት እያደረጉ ነው የተባሉትም 14 ብቻ በመሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ በቂ ክትትል እና ቁጥጥር እያደረገ ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

94.በመሆኑም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች ወደ ኢንዱስትሪው ለመሰማራት የተቀመጠውን አነስተኛ መስፈርት በማሟላት ተመዝግበው እንዲገቡ አለመደረጉ በውጭ አገር ስራ ተቋራጮች የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀምና በፕሮጀክቶች የተሰማሩ ሠራተኞች ሙያዊ መስፈርት አሟልተው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ለመከታተል ያስቸግራል፡፡

ለሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ ያስመዘገቧቸው ሀብቶች በስራ ላይ ስለመሆናቸው ክትትል ማደረጉን በተመለከተ

95.የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው የሰው ኃይል፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ፈቃድ ለወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑንለማረጋገጥ፣ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል የሚያስችል በስራ ቦታው ላይ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ የተመዘገቡት ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በስራ ላይ ስለመሆናቸው በአመታዊ እቅድ ተካቶ የሚጣራበት የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

96.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው የሰው ኃይል፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለተወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን፤ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች ላይ ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ በመመሪያ ቁጥር 648/2013 የተቀመጠ ቢሆንም

የክትትልና ቁጥጥር ስራውን ከ2013-2016 ዓ.ም አጋማሽ በታዩ በአመታዊ ዕቅዶች ላይ አካቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑ፤

- በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ ወስደው በሥራ ላይ ከተሰማሩ በናሙና ተመርጠው ከታዩ 7 ሥራ ተቋራጮች ውስጥ የ3 ሥራ ተቋራጮች በሚሰሯቸው ፕሮጀክቶች ላይ ካሰማሯቸው ማሽነሪዎች 3 ሎደር እና 1ሮለር መለያ (ሰሌዳ) ቁጥር የሌላቸው መሆናቸው፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

97.ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የባለስልጣን መ/ቤታችን የቁጥጥር ዘርፍ ተግባር ፕሮጀክቶችን መከታተልና መቆጣጠር ሲሆን፣ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው የሰው ኃይል፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለተወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን፤ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች ስለመኖራቸዉ በዚሁ ሂደት ክትትል ያደርጋል። በኦዲት ግኝቱ ተመሳሳይ ሁኔታ የባለስልጣን መ/ቤታችን በሚያደርገዉ ቁጥጥር ወቅት ጎልቶ እየታየ ስለነበረ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ ያልተቻለበት ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት የኮንስትራክሽን ቁጥጥር ረቂቅ አዋጅና ደንብ ከላይ በተራ ቁጥር 8 በገለጽነው ሁኔታ አዘጋጅተን ለማፀደቅ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደላኩ እና ለወደፊትም ይህንን ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲያከናውን የኮንስትራክሽን ኦዲትና ኢንስፔክሽን የሥራ ዘርፍ መከፈቱም መልካም አጋጣሚ መሆኑ ታሳቢ ቢደረግ በማለት ገልፀዋል፡፡

98.የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ በሰነድ ያቀረቧቸው ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል ለተወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑንእና በወሰዱት የብቃት ማረጋገጫ ህጋዊ ሆነው እየሰሩ ስለመሆኑ ቁጥጥር አለማድረጉ በተለያዩ የፕሮጀክት ስራዎች የሚከሰቱ ችግሮች ላይ ተጠያቂ የሚሆነውን አካል በመለየት ተገቢው እርምጃ እንዳይወሰድበት ከማድረጉም በላይ ብቃታቸው ሳይረጋገጥ በግንባታ ሥራ ላይ በሚሰማሩ አካላት ህብረተሰቡ እንዲጭበረበር፣ ከአቅማቸው በላይ ሕገ-ወጥ ሰነዶችን በመያዝ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ያለደረጃቸው በመውሰድ ትክክለኛ ደረጃ ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የሚሰራውም ግንባታ ጥራት እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ የክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ ስለመሆኑ

99.የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው (የሰውኃይል፣የስራ ላይ ስልጠና፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች) በሠነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋገጥበትሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

100. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል የተሟላና በሥራ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የስራ ላይ ስልጠና እያገኙ መሆኑን፣ የሚያቀርቧቸውን ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በክትትልና ቁጥጥር በተረጋገጠ ሪፖርት መሰረት እድሳት እያደረገ አለመሆኑ፤ታውቋል፡፡

101. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ እያንዳንዱ መንግስት ተቋም በህግ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት በመኖሩ ምክንያት ከተቋማት ጋር በቅርበት የምንሰራበት አግባብ አለ:: ይህም በመሆኑ ምክንያት በምሳሌ ለማስቀመጥ ያህል ለትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነቶች ውስጥ ለተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች የቴክኒክ ምርመራ በማድረግ ለአገልገሎት ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ማረጋገጫ መስጠት በመሆኑ ይህንን የማረጋገጫ ማስረጃ በመቀበል የምዝገባ አገልግሎት የሚሰጡበት አግባብ ስለመኖሩ ገልፀዋል፡፡

102. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ከባለድርሻ አካላት ጋር የጠበቀ የቴክኖሎጅ ትስስር በመፍጠር ተመሳስለው እየተሰሩ የሚቀርቡ ሀሰተኛ ሰነዶችን የሚከላከልበት ሥርዓት ያልዘረጋ በመሆኑ የስራ ተቋራጮች የሚያቀርቧቸው የሰው ኃይል፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በአካል መኖራቸውን በክትትልና ቁጥጥር ማረጋገጡ አስፈላጊ አይደለም የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

103. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥራ ተቋራጮች ከቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውና ፈቃድ ለማውጣት ያስመዘገቧቸው የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች እና የሰው ሃይል ዝርዝር በእድሳት ወቅት በአካል መኖራቸው አለመረጋገጡ የዘርፉን የፈቃድ አሰጣጥ እና እድሳት አገልግሎት አሰጣጥ ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

በፌደራል እና በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች ያለውን የስራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ በተመለከተ

104. በፌደራል እና በክልሎች፣በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሁም ተመሳሳይ ስታንዳርድ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

105. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ❖ በፌደራል እና በክልሎች፣በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሁም በመመሪያ 648/2013 የፌደራሉ እና የክልሎች ሚና ተለይቶ የተቀመጠ ባለመሆኑ በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ ያወጡ ሥራ ተቋራጮች በድጋሚ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እያወጡ መሆኑ፤
- ❖ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በፌደራል የወጣውን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት (ስታንዳርድ) እንደ ሀገር ወጥና ተመሳሳይ በሆነ መልኩ እየተጠቀሙበት ባለመሆኑ በናሙና የታዩ 3 ክልሎችና 2 ከተማ አስተዳደሮች በራሳቸው እያሻሻሉና ከደረጃ 7 በታች ላሉ ሥራ ተቋራጮች አዳዲስ መመሪያዎችን እያወጡ እየተጠቀሙ መሆናቸው፤ይህንም ለመከታተል እና ለማጣጣም የሚያስችል የተዘረጋ አሰራር አለመኖሩ፤
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮችን የብቃት ማረጋገጫ ከሚሰጡ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ከሚያከናውኑ በየደረጃው ካሉ የክልል/ከተማ አስተዳደር መዋቅሮች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የስራ ግንኙነትም ሆነ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት የሌለው መሆኑ ፤ታውቋል፡፡

106. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣንን ስልጣን፣ ተግባር እና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 524/2015 በአንቀፅ 5 (12) የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባር በግልፅ ያስቀመጠ ቢሆንም በኦዲቱ እንደተረጋገጠው በአንዳንድ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ደንቡ ላይ የተቀመጠውን ወደ ጎን በመተው በተቋማችን የተመዘገቡ ድርጅቶችን

በአስተዳደራዊ ክልላቸው ውስጥ ለመስራት በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ድጋሚ እንደ አዲስ ምዝገባ እንዲያደርጉ እያስገደዱ መሆናቸውን ተቋማችን ከደረሰበት በኋላ ወደ አብዛኛው ክልሎች ቼክሊስት በማዘጋጀት እና አቅጣጫ በማስቀመጥ የባለሙያዎች ቡድን በመላክ የክትትል እና የድጋፍ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን በዚህም ወቅት ከሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ጋር በምንወያይበት ጊዜ በዋናነት በደንቡ ላይ በተቀመጠው መሰረት በፌዴራል የተመዘገቡ ድርጅቶች በየትኛውም የሀገራችን ክፍሎች መስራት እንደሚችሉ፣በመመሪያ 648/2013 እና መመሪያ 19 መሰረት ድርጅቶችን እየመዘገቡ ስለመሆኑ እና ወጥነት ያለው የምዝገባ ስርዓት መኖር እንዳለበት እና በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የፕሮጀክት ምዝገባ ስለማድረጋቸው እንዲሁም ቋሚ የሪፖርት አደራረግ ዙሪያ በደብዳቤ የመደቡትን ባለሙያ የማሳወቅ ስራ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ተሰርቷል እንዲሁም የጋራ መግባባት ተደርሷል በማለት አብራርተዋል፡፡

107. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት በአካል ተገኝተን ማረጋገጥ እንደተቻለው ክልሎች በፌዴራል ደረጃ የወጣውን መመሪያ በራሳቸው እያስተካከሉ (Edit) እያደረጉ እየተጠቀሙ መሆኑን፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር እንጂ ከባለሥልጣኑ ጋር ሥራን የማይገመግሙ መሆኑን፣ የፕሮጀክት ምዝገባ ስራን እንደ ዋና ሥራ ይዘው የማይሰሩ መሆኑን…ወዘተ ያረጋገጥን በመሆኑ እና በፌዴራል እና በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች መካከል ያለውን የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ ሥርዓት ለማስተካከል ሰፊ ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ በቂ ሥራ ተሰርቷል ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

108. በፌደራል እና በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚከናወነው የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ወጥ በሆነ አሰራርና ተመሳሳይ በሆነ መመሪያ አለመመራቱ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ለህገ ወጥና ብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ አድርጓል፡፡

የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ መዘጋጀቱን በተመለከተ

109. ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚሰጣቸው የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ እና የፕሮጀክቶችን ጥራት የሚቆጣጠርበት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅ ይገባል::

110. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎቶችን በተመለከተ በሚ/ር መ/ቤቱ የተዘጋጀ የተገልጋዮች ቻርተር የቀረበ ቢሆንም ቻርተሩ ከተዘጋጀ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑ አሁን እየተሰጠ ያለውን

አገልግሎት የቃኘ የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ ግን ያልተዘጋጀ/ያልተከለሰ/ መሆኑ፣ታውቋል፡፡

111. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በሚ/ር መ/ቤቱ የተዘጋጀዉን የዜጎች ቻርተር እየተጠቀምን የነበርን ብሆንም ነገር ግን የአገልግሎት አሰጣጡ ከማንዋል ወደ ኦንላየን አገልግሎት ስለተሸጋገርን ከዚህ ጋር የሚጣጣም የዜጎች ቻርተር ባለ ስልጣን መ/ቤቱ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል።የአገልግሎት ስታንዳርዶችን አዘጋጅቶ በሥራ ላይ ለማዋል በተለያዩ ጊዜ ጥረት የተደረገ ሲሆን ሙሉ ለሙሉ አጠናቆ በሥራ ላይ ለማዋል የነበሩ አስቸጋሪ ከነበሩት ሁኔታዎች አንዱ የመዋቅር ለውጥ የግድ አስፈላጊ የነበረ በመሆኑ የመዋቅር ጥናቱን በማጥናት አስጸድቆ ወደ ተግባር ለመግባት ከፍተኛ ጊዜ የወሰደ እና በመጨረሻ የፀደቀ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ የጂኤጂ. ምዘና ሥራ አስገዳጅ በሆነ አግባብ ተግባራዊ በደረጉ በድጋሚ የአደረጃጀት ለውጥ ለማድረግ መቻሉ እና ተቋሙ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተፈጠረ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ ተቋቁሞ ወደ ተግባር ለመግባት የተወሰነ ጊዜ መውሰዱ ዋና ዋና ምክንያቶች ሆነው የሚቀመጡ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ግን የስታንዳርድ ዝግጅት ስራውን በማጠናቀቅ ሒደት ላይ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

112. በባለስልጣን መ/ቤቱ አሁን እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት የቃኘ የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ አለማዘጋጀቱ አገልግሎቶች በወቅቱን በዋጀ መልኩ፣በጥራት እንዳይሰጡ ያደርጋል፡፡

በኮንስትራክሽን ዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች የተደረገ ድጋፍን በተመለከተ

113. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሴት ሥራ ተቋራጮችን ተሳትፎ ለማሳደግና የዘርፈብዙ ጉዳዮችን በማካተት በክህሎት ግንባታና አቅም ለመፍጠር እና በሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተለየ ድጋፍ የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

114. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- የሥራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ ለሴት/አካል ጉዳተኛ ሥራ ተቋራጮች በየደረጃው ከሚጠየቀው አመታዊ ተርን ኦቨር ብር መጠን በ15 መቶ እንደሚቀነስላቸው የተቀመጠ ቢሆንም በልዩ ድንጋጌ ከተቀመጠው ከአንቀፅ 27 ውጭ በመመሪያ ቁጥር 648/2013 ዓ.ም የተቀመጡ ሌሎች

መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ተደርጎ በሁሉም ደረጃዎች ብቃት ማረጋገጫው እየተሰጠ ባለመሆኑ ለሴት ሥራ ተቋራጮች አመታዊ ተርን ኦቨር የብር መጠን በ15 መቶ የተቀነሰላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፤

- በኮንስትራክሽን ሥራዎች ልምድ ላላቸው ባለሙያዎች በልዩ ሁኔታ ከሚሰጠው የሥራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫ ለሴት ሥራ ተቋራጮች ሁለት ዓመት ዝቅ ተደርጎ የተሰጠ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም የተሰጣቸው ሴት ሥራ ተቋራጮች ማስረጃ አልቀረበም፤
- በአምስት አመት የስትራቴጂክ ዕቅድ(2013-0217) ላይ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሴቶችን የሙያ እና የአመራር ተሳትፎ ለማሳደግ በተለየ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የድጋፍና ክትትል አሰራር ተግባራዊ እንደሚያደርግ ያስቀመጠ ቢሆንም ለሴት ባለሙያዎች የተደረገ ልዩ ድጋፍ፣ ሥልጠና እና ሌሎች የተሰሩ ሥራዎች ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች እና አካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍ ስለመደረጉ በናሙና በታዩ 7 ሥራ ተቋራጮች በሚያከናውኗቸው ፕሮጀክቶች ከዝቅተኛ ሠራተኞች ውጪ የሴት ፕሮጀክት ማናጀሮችንም ሆነ ከፍተኛ ባለሙያዎችን ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ፤
- በየበጀ ዓመቱ በባለሥልጣን መ/ቤቱ አገልግሎት ያገኙ ሴት ባለሙያዎች መኖራቸውን በቁጥር ከመግለፅ ውጭ በሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ክፍል የተደረገ የድጋፍና ክትትል ስራ ስለመኖሩ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ ፣በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ በመመሪያ 648/2013 አንቀፅ 27 ለሴቶች ተጠቃሚነት በተቀመጠው አንቀፅ መሰረት በሽግግር ድንጋጌው ምክንያት በቀድሞ መመሪያ 19 እያደሱ በመሆናቸው የ15 በመቶ የተርን ኦቨር ቅነሳ እድልን ለመጠቀም እያመለከቱ ባይሆንም ይህ የእፎይታ ግዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ድርጅቶች በመመሪያ 648/2013 መመዝገብ ስለሚገባ የቅነሳ ዕድሉን ሴቶች በሰፊው እንደሚጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ ከወንዶች በሁለት ዓመት ያነሰ የስራ ልምድ በማቅረብ የተቀመጠውን ዕድል ሴት የስራ ተቋራጮች እየተጠቀሙ ያለ ቢሆንም በተወሰደው የስራ ተቋራጮች ናሙና ውስጥ ባለመውደቃቸው እና በ E-service ሪፖርት አወጣጥ ችግር የሴቶችን ብቻ ለይቶ ማውጣት ላይ ክፍተት

በመኖሩ በአሁኑ ሰዓት እየተሰራበት ያለ ቢሆንም እድሉን በተጠቀሙት ብዛት ልክ ዝርዝራቸው ያልተገኘ በመሆኑ መረጃውን ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ እና የሴት ሥራ ተቋራጮችን ተሳትፎ ለማሳደግና የዘርፈ-ብዙ ጉዳዮችን በማካተት በክህሎት ግንባታና አቅም ለመፍጠር እና በሚሰጡ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተለየ ድጋፍ የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት በመመሪያው እነሱን ለመደገፍ የተቀመጠ ሲሆን በቀጣይ በተለያዩ መድረኮች እነሱን የሚያሳትፍ መመሪያ እንዳለ የማሳወቅ ስራ ይከናወናል፤አዲስ የወጣው መመሪያ 648/2013 ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን ወደ ስራ የሚያስገቡመሆኑን እና ትኩረት እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡

116. የባለስልጣኑ ሃላፊዎች ይህን ቢሉም በኮንስትራክሽን ዘርፍ ሴቶችን ለመደገፍ መመሪያ ከማዘጋጀት ውጭ በዘርፉ ያለውን የፆታ ልዩነት ሊያጠብ በሚችል መልኩ በዕቅዳቸው አካትተው ተግባራዊ ባለማድረጋቸው እና ለሴቶች ሰጥተናል ያሉትን ማስረጃ ባለማቅረባቸው ተገቢ ሥራዎች ተሰርተዋል ብሎ ለመቀበል ያዳግተናል፡፡

117. ሴት ባለሙያዎች ወደ ኮንስትራክሽን ዘርፉ በብዛት እንዲመጡ ድጋፍ አለመደረጉ ልምድ ያላቸው ሴት ባለሙዎች ወደ ሰራ ተቋራጭነት እንዳይመጡ እና በኢንዱስትሪው ውስጥ ሚና እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡

IV. የሥራ ተቋራጮችንና ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤

በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በመመዝገብ ቁጥጥር ማደረጉን በተመለከተ

118. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና የመንግስት ፕሮጀክቶችን እንደየምድባቸው መዝግቦ በመያዝ ሊቆጣጣር ይገባል፡፡

119. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ የግል እና የመንግስት ኮንስትራክሽንፕሮጀክቶችን በደንብ ቁጥር439/2011፣*524/2015 እና መመሪያ ቁጥር648/2013 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት* እንደየምድባቸው መዝግቦ በመያዝ የፕሮጀክቶችን መረጃ ለቁጥጥርና ክትትል ሥራው ግብዓት በሚሆን መልኩ የተደራጀ የፕሮጀክቶች መረጃ ያልያዘ መሆኑ፣
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች ስላሉ ፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝና ክትትል ግልፅ የሆነ የአሰራር ሥርዓት ያላስቀመጠ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

120. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የግንባታ ፕሮጀክቶች ለመመዝብ የሚያስችል የኢ-ሰርቪስ ምዝገባ ስርዓት ዘርግቶ ፕሮጀክቶችን ከመመዝገቡም በተጨማሪ በማንዋሉም ወደ መስክ በመሄድ የተመዘገቡ ፕሮጀክቶች አደራጅቶ በመያዝ ለቁጥጥር ሥራ በግብዓትነት እየተጠቀምንበት ቢሆንም እንኳ በሚፈለገው ደረጃ ያልተደራጀ ስለሆነ ለቀጣይ በተጠናከረ ሁኔታ እንሰራለን፡፡በሌላ በኩል ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከክልሎች ሆነ ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በቀጥታ የሚገናኝበት የህግ ሂደት የሌለ ቢሆንም የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ 648/2013 በአንቀፅ 33/7 ከሌሎች ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ፕሮጀክቶችን እንደሚሰራ በተቀመጠው መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝ ዙሪያ በጋር በመቀናጀት እየሰራ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ ፕሮጀክቶችን በኢ-ሰርቪስና በማንዋል መንገድ ወደ መስክ ሄዶ በመመዝገብና አደራጅቶ በመያዝ

ለቁጥጥር ሥራበግብዓትነት እየተጠቀምንበት ነው የሚለው እና በፕሮጀክቶች መረጃ አያያዝ ዙሪያ ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት እየሰራ እንገኛለን የሚለው ምላሽ በኦዲቱ ወቅት ለኦዲቱ የሚፈለገው የፕሮጀክቶች መረጃ ባለመገኘቱ ከዋና ኦዲተር መ/ቤት ለተለያዩ የፕሮጀክት ባለቤቶችና ባለድርሻ አካላት በተፃፈ ደብዳቤ የተቋረጡ የፕሮጀክቶች መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ ናሙና ተመርጦ የተሰራ በመሆኑ፣ የፕሮጀክቶች መረጃ በየጊዜው ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሁኔታ እንዲያሳይ(update) እየተደረገ የማይያዝ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

121. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ ፕሮጀክቶችን መዝግቦ በተደራጀ መልኩ አለመያዙ የክትትልና ቁጥጥር ስራውን በአገሪቱ ባሉ ፕሮጀክቶች ልክ አቅዶ እንዳይንቀሳቀስ ከማደረጉም በተጨማሪ እንደሀገር የፕሮጀክቶች መረጃ ክፍተት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አሰሪ መ/ቤቶች ወቅታዊ መረጃዎችን ለባለሥልጣኑ በየጊዜው ማሳወቃቸውን በተመለከተ

122. ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የአፈጻጸም መረጃዎች (የተጠናቀቁ፣ የዘገዩ፣ የተቋረጡ...) መሆናቸውን አሰሪ መ/ቤቶች በየስድስት ወር ማሳወቃቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

123. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የአፈጻጸም ደረጃና ወቅታዊ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ አሰሪ መ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ በየስድስት ወር እያሳወቁ ባለመሆኑ ፕሮጀክቶች በውለታቸው መሰረት እየተከናወኑ ያሉ፣ የዘገዩ ፣የተቋረጡ እና የተጠናቀቁ መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ መረጃዎች ተይዘው በመረጃው መሰረት ጠንካራ ክትትል እየተደረገ አለመሆኑ፤ታውቋል፡፡

124. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመዘገባቸውን ፕሮጀክቶች በውላቸው መሰረት እየተከናወኑ ያሉ፣ የዘገዩ፣ የተቋረጡ እና የተጠናቀቁ መሆናቸውን የሚያሳዩ መሆናቸውን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ቢገኝም የሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቶች በሚፈለገው ደረጃ ያልተደረጀ ሲሆን በቀጣይ የሁሉንም የግንባታ ፕሮጀክቶች በተደረጀ ሁኔታ እንሰራለን፡፡በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ

የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን የሚያስገነቡ መ/ቤቶች የፕሮጀክቶችን የአፈጻጸም ደረጃና ያሉበትን ሁኔታ በየስድስት ወሩ እንዲያሳውቁ ክትትል እየተደረገ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ አልተፈጸመም፡፡

125. በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ወቅታዊ ያሉበትን ደረጃ መሰረት በማድረግ ክትትል አለመደረጉ ፕሮጀክቶች ከውለታ ውጪ ለረጅም ጊዜ በመዘግየትና ተቋርጠው በመቆየት ለመንግስት ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት፣ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር እንዲጋለጡ ያደረገ ሲሆን የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ደግሞ በወቅቱ ጥራት ያለው አገልግሎት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ቋት መደራጀቱን በተመለከተ

126. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ታዕማኒነት ያለው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ቋት ወይም ዳታ ቤዝ በማደራጀት መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡

127. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት እንደተቻለው፡-

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ታዕማኒነት ያለው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ቋት(database) በማደራጀት መረጃ እየያዘ አለመሆኑ፤
- የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች ማኅደር ግራውንድ ውስጥ በመቀመጡና ለፍሳሽ በመጋለጡ አገልግሎት መስጠት በማይችልበት ደረጃ ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፤
- የሥራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ መሰጠት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 2015 መጨረሻ በኤክሴልና በሌሎች አክሰስ ፋይሎች ተመዝግበው የተያዙ የሥራ ተቋራጮች ፕሮፋይል በቀላሉ በሚገኙበት ሁኔታ በየዘርፋቸውና በወሰዱበት የበጀት አመት አዲስ፣ ደረጃ እድገት እና እድሳት በሚል በሚፈለጉበት ጊዜ በቀላሉ በሚገኙበት ሁኔታ ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፤
- በአንድ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ/ ተሽከርካሪ በሐሰተኛ ሊብሬ በድጋሚ ሌሎች ፈቃድ እንዳያወጡ፣ አንድ ባለሙያ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሥራ ተቋራጮች የቅጥር ውል እንዳይፈፀም ለማጣራት የሚያስችለው ዘመናዊ የመረጃ ማጣሪያ የአሰራር ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤

❖ የኢ-ሰርቪስ አገልግሎት ከተጀመረ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮችን ማስረጃ ባካፕ ሲስተም የሌለው በመሆኑ ማስረጃዎች ከሲስተም ሲጠፉ ማስረጃዎችን ለማግኘት(Recover) ማድረግ አለመቻሉ፣ ታውቋል፡፡

128. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ባለስልጣን መ/ቤቱ የኢንዱስትሪውን የመረጃ ቋት ለማዘጋጀት ከኢንፎርመሽን መረብ ደህንነት(ኢንሳ) ጋር መግባቢያ የተፈረመ ቢሆንም የማልማቱን ስራ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችንም ባካተተ መልኩ ማልማት ስለሚያስፈልግና ለክልሎችም ይሁን ለከተማ አስተዳደር የማልማት ሥልጣን ያለው ሚ/ር መ/ቤቱ በመሆኑ የከተማና የመሰረተ ልማት ሚኒስቴር እያለማ በመሆኑ ምክንያት ባላስልጣን መ/ቤቱ ማልማት አልቻለም ሆኖም ግን አሁን በሚ/ር መ/ቤቱ እየለማ ይገኛል፡፡

129. ከዚህ በተጨማሪ በመንግስታዊ ተቋማት የሚያስፈልጉ እንደ ፎርጅድና ሌሎችንም እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን ለመከላከል እና ሌሎች ሲስተሞች የማልማት ስራዎች እንደ ሃገር በኢኖቬሽን ሚኒስቴር መሆን እንደለበት ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት በተላለፈው ሰርኩላር ደብዳቤ መሰረት በዕቅድ የተያዙ ሶፍትዌሮችን/ሲስተሞችን ማልማት ባይቻልም አሁን ግን ከጠ/ሚ/ር ፅ/ቤት ከመጡ ባለሙያዎች ጋር በተደረገ የጋራ ውይይት መግባባት ላይ በተደረሰው መሰረት ከኢንሳና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ሆነን አልምተን ሪፖርት ማድረግ እንዳለብን በደብዳቤ ባሳወቁን መሰረት ከተቋማቱ ጋር በመረጃ ቋት(database) እና በሌሎች ቴክኖሎጅዎች ዙሪያ ለማልማት መግባባት ላይ ተደርሶ ሥራው ተጀምሯል፡፡ከጠ/ሚ/ጽ/ቤት የተጻፈልን ደብዳቤ ያያዝን መሆናችን እንገልጻለን፡፡

130. ከኢ-ሰርቪስ በሚደረገው ምዝገባ አማካኝነት ሲስተሙ እራሱ በተደራጀና በሚፈለገው ሁኔታ ሪፖርቱን እንዲወጣ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና ኢ-ሰርቪሱን እያለማ ከለው ድርጅት ጋር በተደጋጋሚ በተደረገው ውይይት መሰረት ሲስተሙ የተመዘገቡና ብቃት ማረጋገጫ ያገኙ ባለሙያዎች እና የኩባንያዎች ሪፖርቶች በተደራጀ መልኩ እያወጣን እንገኛለን፡፡ባካፕ መያዝን በተመለከተ በኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሰርቨር ላይ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም ከተገዛው የራሳችን የክላውድ ሰርቨር ላይ እና በሀርድ ኮፒ በመያዝ ላይ እንገኛለን በማለት አብራርተዋል፡፡

131. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በኦዲቱ ወቅት የኩባንያዎች ፕሮፋይል በየዘርፋቸው፣ በየደረጃቸው፣ በፆታቸው ...ወዘተ በሚፈለገው

መልኩ የተደራጀ ሪፖርት የማይሠጥ መሆኑን በተለያ ጊዜ የጠየቅናቸው የኩባንያዎች ፕሮፋይል ለመለየት በማይቻል ሁኔታ ተቀላቅለው የቀረቡ በመሆኑ የኩባንያዎችን ሪፖርቶች በተደራጀ መልኩ እያወጣን እንገኛለን የሚለውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል::

132. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ የመረጃ ቋት(database) ተደራጅቶ አለመያዙ በሀርድ ኮፒ ያሉ የባለሙያዎችና የድርጅቶች ፕሮፋይሎች በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ከማድረጉም በተጨማሪ መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ ተደራሽ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

ከባለድርሻ አካላት ጋር ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ መደረጉን በተመለከተ

133. ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት (ከገንዘብ ሚ/ር፣ ከፕላንና ልማት ሚ/ር፣ ከፕሮጀክት ባለቤቶች፣ ከትምህርት ተቋማት…ወዘተ) ጋር ወቅቱን የጠበቀ ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

134. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚያደርገው ቅንጅታዊ አሰራርና ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ ክፍተት ያለው በመሆኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- ❖ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ካሉ የትምህርት ተቋማት ጋር የተክኖሎጅ ትስስር የሌለው በመሆኑ ፎርጅድ የትምህርት ማስረጃዎችን የሚያጣራበት አሰራር አለመኖሩ፤
- ❖ የግል የሠራተኞችን ቅጥር ከሚፈፅሙ የመንግስት ተቋማት ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑና በእየለቱ የሚመጡ የሠራተኛ የቅጥር ውሎችን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥበት መንገድ የሌለ መሆኑ ፤
- ❖ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ሊናበብ የሚችል የቴክኖሎጅ ትስስር የሌለው በመሆኑ የስራ ተቋራጮች የሚቀጥሯቸው ባለሙያዎች ከአንድ በላይ ለሆኑ ድርጅቶች የሚቀጠሩ መሆናቸው፤እንዲሁም የሥራ ተቋራጮች ምዝገባ ድግግሞሽ እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑ፤

- ❖ በሀገር ደረጃ ያሉ ፕሮጀክቶችን ትክክለኛ መረጃ ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፤ታውቋል፡፡

135. ስለጉዳዩ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በኢ-ሰርቪስ አማካኝነት በሪፖርት መልክ እየተዘጋጀ እንዲወጣ ከኢኖቬሽን ሚኒስቴር እና ኢ-ሰርቪስን ካለማው ድርጅት ጋር እየተሰራ ይገኛል፡፡ይህ ስራ ቀደም ተብሎ ከመረጃ ቋት ከማልማት ጋር አብሮ እንዲካተት የታሰበ ስራ ሲሆን በዚህ መሰረት የትምህርት ተቋማትን የማቀናጀቱ ስራ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እያለማ ካለው ጋር እየተሰራ ይገኛል፡፡ ነገር ግን እኛ እራሳችን የሚንሰጠውን የብቃት ማረጋጋጫ ትክከለኛነት ማረጋገጫ ባር ኮድ (ፎርጂድ ማረጋገጫ) በኢኖቬሽን ሚኒስቴር በኩል ኢ-ሰርቪስን ካለማው ድርጅት እንዲያለማልን እየተደረገ ነው፡፡የሠራተኛ ቅጥር ውሎችን ትክክለኛነት የምናረጋግጠው ቀጣሪው አካል ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ መቀጠሩን ሲያረጋግጥ ብቻ መሆኑን እየገለፅን ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ያለውን ትስስር በተመለከተ ደግሞ ችግሩን ለመፍታት ከኢንፎርመሽን መረብ ደህንነት(ኢንሳ) ጋር መግባቢያ የተፈረመ ቢሆንም የማልማቱን ሰራ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲያለማው ውሳኔ በተላለፈው መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመልማት ላይ ይገኛል በማለት አብራርተዋል፡፡

136. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ አለማድረጉ ሥራ ተቋራጮች ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ ማስረጃ አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረጉም በተጨማሪ አሁን በሀገር ደረጃ ያሉ ፕሮጀክቶችን ቁጥር ትክክለኛ መረጃ እና እያንዳንዱ ፕሮጀክት ያለበትን ደረጃ አውቆ ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ (Conclusion)

137. በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የፌደራል መንግስት የተቋረጡ ፕሮጀክቶች፣ የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ እና ሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ቁጥጥርና ክትትል አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

- ❖ በፌዴራል በጀት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን የያዙ ሥራ ተቋራጮች የያዙትን ፕሮጀክት ሳያጠናቅቁ ወይም አፈፃፀማቸው ሳይታይ በሌላ ጨረታ ላይ እንዳይወዳደሩ የሚከለክል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ቁጥጥርና ክትትል ባለመደረጉ የውል ዋጋቸው ብር10,764,373,751.02 የሆነ 12 ፕሮጀክቶች በ2 ሥራ ተቋራጮች የተያዙ መሆናቸው ታይታል፡፡
- ❖ የፕሮጀክቶች መቋረጥ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብ ብክነት ሊቀንስ የሚችል ሥራ አስቀድሞ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካለት በቅንጅት ባለመሰራቱ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ በመጀመሪያ ውለታቸው ሳይጠናቀቁ በሌላ ጨረታ ወደ ግንባታ የገቡ 13 ፕሮጀክቶች በመንግስት ላይ ያስከተሉት ተጨማሪ ወጪ በድምሩ ብር **16,681,131,031.64** መሆኑ ታውቋል፡፡
- ❖ ፕሮጀክቶች በሚቋረጡበት ጊዜ የፕሮጀክት ባለቤቶች ተግባርና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እና በባለሥልጣኑም በኩል የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ክትትል ባለመደረጉ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ12 ፕሮጀክቶች ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶች ተመዝግበው ያልተያዙ ሲሆን የ27 ፕሮጀክቶች ደግሞ በሰነድ ደረጃ ተመዝግበው የተያዙ ቢሆንም ንብረቶቹ በተገቢው ሁኔታ ተጠብቀው ያልተያዙ መሆናቸው ታውቋል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በውስን ፕሮጀክቶች ላይ ስራዎችን ያከናወነ ቢሆንም የሀገሪቱን ፕሮጀክቶች እንደሚከታታልና እንደሚቆጣጠር አካል ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ጠንካራ ሥራ ባለመስራቱ 4 ፕሮጀክቶች የማጠናቀቅያ ሥራ (Finishing) ሲቀራቸው ተቋርጠው ከ2ዓመት በላይ በመቆየታቸው በጣሪያ መገንጠል እና የጣሪያ ፍሳሽ

ማስወገጃ (joint Expansion) ባለመገጠሙ ምክንያት ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ ታይታል፡፡

❖ በተቋረጡ ፕሮጀክቶች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት ክፍተት በመኖሩ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ የ3 ፕሮጀክቶች ብር 471,182,026.54 (አራት መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ሃያ ስድስት ከ54/100 ብር) በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ፣ እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው በ35 ፕሮጀክቶች ብር 1,940,362,449.81 (አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሃያ ሺ ሶስት መቶ አምሳ አንድ ከ87/100 ብር) በአጠቃላይ የ38 ፕሮጀክቶች ብር **2,411,544,476.35 (ሁለት ቢሊዮን አራት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሁለት ሺ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ከ41/100 ብር)** የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ያልተወረሰ /ገቢ/ ያልተደረገ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

❖ በናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለ25 ፕሮጀክቶች ከተከፈለው የቅድመ ክፍያ (Advance Payments) ብር **3,220,090,230.36** ውስጥ የ6 ፕሮጀክቶች በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያሉ ብር 672,540,236.97 እና በክስ ሂደት ላይ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው የ19 ፕሮጀክቶች ብር 1,795,255,090.20 በድምሩ ብር **2,467,795,327.17** ተመላሽ ተደርጎ ለሌሎች የልማት ስራዎች እንዲውል ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እንደ ሀገር ከተሰጠው የግልም ሆነ የመንግስት ፕሮጀክቶችን ለመቆጣጠር የሚያስችል የሰው ሃይል ያላሟላ መሆኑ፣ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በወሰዱት የብቃት ማረጋገጫ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ የሚችል የሥራ መደብ በመዋቅሩ ውስጥ ያልተካተተ እና ለስራውም የተመደበ የሰው ኃይል የሌለ መሆኑ ለመገንዘብ ተችላል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ወደ አስር የሚሆኑ ጥናቶችን ብር 17,789,840.81 (አስራ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ አርባ ከ81/100 ብር) ወጪ አድርጎ ያስጠና ቢሆንም በኦዲት አካባቢው ዙሪያ በተጠኑ ጥናቶች መሻሻል የሚገባቸው ተብለው ከተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ውስጥ ተግባራዊ ያልተደረጉ መኖራቸው ተገንዝበናል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በባህላዊ ቅርሶች፣ በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በተደረገ

የአካል ምልከታና ቃለ መጠይቅ በናሙና በታዩ ግንባታ ላይ ያሉ 7 ፕሮጀክቶችን የሚሰሩ ሥራ ተቋራጮች የቅድመ መከላከል ሥራዎችን አሟልተው እየሰሩ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገላጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ ባለመያዙ ናሙናዎችን መርጦ በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው ፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ስለመካተታቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ እየወሰዱ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው የመቆጣጠር ኃላፊነት መሰረት የፕሮጀክት ባለቤቶችን እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክት ቁጥጥርና አፈፃፀም መመሪያ፣ ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት መመሪያ፣ የፕሮጀክት ምዝገባን በተመለከተ የባለሥልጣኑን እና የክልሎችን ሚና በግልፅ ለይቶ የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው በመስፈርትነት የተቀመጠውን የሰው ሀይል፣የተሽከርካሪና ማሽነሪ መጠን በከፊል ሳያሟሉ፣የማሽነሪ ቴክኒካል ምርመራ ማስረጃ ሳያቀርቡ እና ሳያድሱ፣የባለሙያዎች የስራ ልምድ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ማስረጃ ሳያቀርቡ፣የደረጃ ማሻሻያ ሲያደርጉ የድርጅቱን ተርን ኦቨር ማስረጃ ሳያቀርቡ እና የሌላ ሰው መታወቂያ በማቅረብ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ሥራ ተቋራጮች መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ❖ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ 261 የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች እንዳሉ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን የተገኘ መረጃ የሚያሳይ ቢሆንም ከ14 ሥራ ተቋራጮች ውጪ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሁሉንም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በምዝገባ መመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል እያደረገ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው የሰው ኃይል፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ለተወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን፣ ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል በአመታዊ እቅዱ አካቶ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ባለመሆኑ በናሙና በታዩ ፕሮጀክቶች ላይ መለያ(ሰሌዳ) ቁጥር የሌላቸው ማሽነሪዎች የተገኙ መሆናቸው ለመገንዘብ ተችላል፡፡
- የሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል የተሟላና በሥራ ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የስራ ላይ ስልጠና እያገኙ መሆኑን፣ የሚያቀርቧቸውን ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በሰነድ የሚያረጋግጥ ቢሆንም በአካል መኖራቸውን በክትትልና ቁጥጥር በተረጋገጠ ሪፖርት መሰረት እድሳት እያደረገ አለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በፌደራል፣ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሁም የፌደራሉ እና የክልሎች ሚና ተለይቶ የተቀመጠ ባለመሆኑ በፌደራል ደረጃ የብቃት ማረጋገጫ ያወጡ ሥራ ተቋራጮች በድጋሚ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እያወጡ ከአንድ በላይ የሆኑ የብቃት ማረጋገጫዎችን ይዘው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
- በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚሰጡ የብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎቶችን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ የተገልጋዮች ቻርተር የቀረበ ቢሆንም ቻርተሩ ከተዘጋጀ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ በመሆኑ አሁን እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት የቃኘ የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመመሪያ ቁጥር 648/2013 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የሚያወጡ ስራ ተቋራጮች አካል ጉዳተኛ/ሴት ከሆኑ በዘርፉ ልምድ ላላቸው ባለሙያዎች በልዩ ሁኔታ ከሚሰጠው የሥራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫ ሁለት ዓመት እና በየደረጃው ከሚጠየቀው አመታዊ ተርን ኦቨር ብር መጠን በ15 መቶ እንደሚቀንስላቸው የተቀመጠ ቢሆንም ለሴት/ለአካል ጉዳተኛ ባለሙያዎች የተደረገ ድጋፍ ስለመኖሩ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ የግል እና የመንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን በደንብ ቁጥር439/2011፣ 524/2015 እና መመሪያ ቁጥር 648/2013 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት እንደየምድባቸው መዝግቦ በመያዝ የፕሮጀክቶችን መረጃ ለቁጥጥርና ክትትል ሥራው ግብዓት በሚሆን መልኩ አደራጅቶ ያልያዘ መሆኑ ታይቷል፡፡

❖ በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የአፈጻጸም ደረጃና ወቅታዊ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ አስሪ መ/ቤቶች ለባለስልጣን መ/ቤቱ በየስድስት ወር እያሳወቁ ባለመሆኑ ፕሮጀክቶች በውለታቸው መሰረት እየተከናወኑ ያሉ፣ የዘገዩ፣ የተቋረጡ እና የተጠናቀቁ መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ መረጃዎች ተደራጅተው ተይዘው በመረጃው መሰረት ክትትል እየተደረገ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በታገዘ የመረጃ ቋት (database) አደራጅቶ የያዘ ባለመሆኑ በሀርድ ኮፒ ያሉ የባለሙያዎችና የድርጅቶች ፕሮፋይሎች በብልሽት እየተጋለጡ ያሉ ከመሆኑም በተጨማሪ የኢንዱስትሪው መረጃ በተደራጀ መልኩ ተደራሽ አለመሆኑ ታውቃል፡፡

❖ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሊናበብ የሚችል የቴክኖሎጂ ትስስር እና ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ የሌለው በመሆኑ በሥራ ተቋራጮች የሚቀርቡ ሰነዶችን በማጣራት እና በፕሮጀክቶች ክትትል በኩል እየገጠሙ ያሉ ችግሮችን ማስቀረት ያልተቻለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳብ (Reccommendation)

138. ለፕሮጀክቶች ቁጥጥርና ክትትል፣ ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ምዝገባ እና ለሰራተኞች የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ቁጥጥርና ክትትል የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ብለን ያመንባቸውን የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንግሰት በጀት የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ በመያዝ በፕሮጀክቶች መቋረጥ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ የገንዘብና የንብረት ብክነት እና የአገልግሎት አቅርቦት ችግር ከመሰረቱ ሊፈታ የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ኃላፊነታቸውን የማይወጡ የፕሮጀክት ባለቤቶች እና ሥራ ተቋራጮች ላይ የእርምት እርምጃ የሚወስድበት አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለፕሮጀክቶች መልካም አፈፃፀም ሲባል የመንግስትን ፕሮጀክት የሚሰሩ ተቋራጮች አስቀድመው በወሰዱት ፕሮጀክት ላይ ያሳዩት አፈፃፀም በቀጣይ የሚወዳደሩበት ፕሮጀክት ለማሸነፍ እንደመስፈርት እንዲገባ በማድረግ ተቋራጮችን የያዙትን ፕሮጀክት ጊዜውንና ጥራቱን ጠብቀው በኃላፊነት መስራት ለቀጣይ ሥራዎች ዋስትና መሆኑን እንዲገነዘቡ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘርጋ የሚያስችለውን የህግ ማዕቀፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆኑ ማዘጋጀት ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር እየተጋለጡ በመሆኑ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይቶችን በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በገቡት ውል መሰረት ግዴታቸውን ሳይወጡ ፕሮጀክቶችን አቋርጠው ከሄዱ ሥራ ተቋራጮች ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበት የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና (PerformanceGuarantees)ገቢ እንዲደረግ ከፕሮጀክት ባለቤቶች እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ጠንካራ የክትትል ሥራ መስራት ይኖርበታል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጠንካራ ክትትል በማድረግ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈለው የቅድመ ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ለሌሎች የልማት ሥራዎች እንዲውል ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፕሮጀክቶችም ሆነ በሥራ ተቋራጮች ቁጥጥርና ክትትል ስራ ላይ የታዩ ክፍተቶችን ሊሞላ የሚችል የተደራጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል አሟልቶ ሥራዎችን ሊያከናውን ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ገንዘብ አውጥቶ ያስጠናቸውን ጥናቶች ወደ መመሪያና ማንዋሎች በመቀየር በተጠናላቸው አላማ መሰረት እንዲተገበሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር 439/2011 እና 524/2015 በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በአካባቢ ፣በባህላዊ ቅርሶች፣በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ እየደረሰ ያለውን ከፍተኛ ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግል ድርጅቶች በሚያሰሯቸው የፕሮጀክት ውሎች ላይ የአካባቢን፣ የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚመለከቱ ጉዳዮች ተካተው ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የእርምት እርምጃ የሚወስድበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እንደ ሀገር በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች ላይ እየደረሱ ያሉ የአደጋ አጋጣሚዎችን ክትትል በማድረግ ገለጭ በሆነ መልኩ በየትኛው ፕሮጀክት ምን አይነት አደጋ እንደደረሰ የሚያሳይ የተደራጀ መረጃ በመያዝ ተጎጅዎች ወቅቱን የጠበቀ መፍትሔ እዲያገኙ እና የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊሰራ ይገባል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደንብ ቁጥር439/2011እና524/2015 በተሰጠው የመቆጣጠር ኃላፊነት መሰረት የፕሮጀክት ባለቤቶችን እንደየጥፋታቸው ደረጃ ተጠያቂ ማድረግ የሚያስችል የፕሮጀክት ቁጥጥርና አፈፃፀም መመሪያ፣ለሥራ ተቋራጮች ብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠ በኋላ ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት መመሪያ፣የባለሥልጣኑን እና የክልሎችን ሚና በግልፅ ለይቶ የሚያስቀምጥ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ አዘጋጅቶ በማፅደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣ በህንፃ፣ በመንገድ ሥራ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥና ደረጃ ሲያድጉ በየደረጃው በአነስተኛ መስፈርትነት የተቀመጠውን የማሽነሪና የተሽከርካሪ፣የሰው ኃይል፣ አመታዊ ተርንአቨር....ወዘተ ያሟሉ መሆኑ፣ ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት የሚቀርቡ የሰነድ ማስጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና የታዩ ክፍተቶችን ለማረም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በጠቅላላ፣በህንፃ፣በመንገድ እና በልዩ ሥራ ተቋራጭነት ዘርፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙ ሁሉም የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የብቃት ማረጋገጫ በመስጠት እና በሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ላይ ለውጭ አገር ድርጅቶች የተቀመጡ ቅድመ ሆኔታዎችን(የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን እያሳተፉ መሆኑን፣በዘርፉ የቴክኖሎጅ ወይም ዕውቀት ሽግግር መደረጉን...ወዘተ) በተመለከተ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም ዓይነት የስራ ተቋራጭነት የብቃት ማረጋገጫ ለመውሰድ እና ደረጃቸውን ለማሳደግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎችና የሰው ኃይል በአካል መኖራቸውን የሚያረጋግጥበት፣ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ፣እንዲሁም የብቃት ማረጋገጫቸውን ለሌላ አካል አሳልፈው የሚሰጡ የስራ ተቋራጮችን በቅድሚያ ለመከላከል የሚያስችል፤ ወደ ህገ ወጥ ሥራ ገብተው ሲገኙም እርምጃ የሚወሰድበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ እድሳት ለማድረግ የሚመጡ ሥራ ተቋራጮች በሰነድ የሚያቀርቧቸው ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የሰው ኃይል በአካል መኖራቸው በክትትልና ቁጥጥር ሪፖርት ከተረጋገጠ በኋላ እድሳት ሊያድርግ ይገባል፡፡
- በፌደራል እና በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ በሆነ መልኩ ለመምራት የሚያስችል

ተመሳሳይ ስታንዳርድ በማዘጋጀት እና ክልሎች ወጥ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙበት ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በባለስልጣን መ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት እየተሰጠ ያለውን የብቃት አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት የቃኘ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ዘርፉ እንዲጠቀምበት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በኮንስትራክሽን ዘርፉ ልምድ ያላቸው አካል ጉዳተኛ/ሴት ባለሙያዎች በመመሪያው ልዩ ድንጋጌ መሰረት የሥራ ተቋራጭነት ብቃት ማረጋገጫውን በመውሰድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
- የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ መረጃ እንደሀገር መዝግቦ በመያዝ ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የፌደራሉን እና የክልሎችን/ የከተማ አስተዳደሮች ሚና የለየ፣የሥራ ተቋራጮችን መብትና ግዴታ በግልፅ ያስቀመጠ አስገዳጅ የፕሮጀክት ምዝገባ መመሪያ በማዘጋጀት እና ተግባራዊ በማድረግ አሁን እየታየ ያለውን የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ክፍተት፣ ብልሹ አሰራር እና እንደሀገር ያለውን የተደራጀ መረጃ እጥረት እንዲቀረፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በፌዴራል መንግስት በጀት ፕሮጀክቶችን የሚገነቡ አሰሪ መ/ቤቶች ፕሮጀክቶቻቸው ያሉበትን ወቅታዊ ደረጃ የሚያሳይ መረጃ የሚያሳውቁበት አሰራር ዘርግቶ መረጃዎችን በመያዝ እና በመረጃው መሰረት ጠንካራ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ መንግስትን ከከፍተኛ የገንዘብ ብክነት በመታደግ ተጠቃሚዎችም ከፕሮጀክቶቹ ማግኘት ያለባቸውን አገልግሎት እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን አጠቃላይ መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አንድ ወጥ የመረጃ ቋት(database) አደራጅቶ በመያዝ እራሱም ሆነ ሌሎች የመረጃው ተጠቃሚ አካላት እንዲጠቀሙበት በማድረግ፣በሀርድ ኮፒ ያሉትን ወደ ሶፍት ኮፒ ቀይሮ በመያዝ እና በሀርድ ኮፒ ያሉትንም ከብልሽት እንዲጠበቁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት አካላት ጋር ዘመናዊ የተክኖሎጅ ትስስር እና የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በጋራ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን መቅረፍ ይኖርበታል፡፡

አባሪ 1፡ የባለሥልጣን መ/ቤቱ አደረጃጀት ሥዕላዊ መግለጫ



አባሪ-2፡ *መመዘኛ መስፈርቶች*

የኦዲት ጭብጥ (Audit Issue)	*መመዘኛ መስፈርቶች*(Criteria)
I. በባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተቋረጡ የፌደራል መንግስት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምዝገባና ቁጥጥር ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋናውጤታማ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፤	1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል በጀት የሚሰሩ የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ከመጀመራቸው በፊት የቅድመ አዋጭነት እና የአዋጭነት ጥናት(preliminary and feasibility study) አስጠንተው ያስፀደቁ ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 15*
	2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው በተቋረጡ ፕሮጀክቶች የታዩ የአፈፃፀም ግድፈቶችን ተከትሎ በመንግስት ሀብት ላይ እየፈጠረ ያለውን ብክነት እና የፕሮጀክቶች ባለቤቶችም ተግባርና ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ክትትል በማድረግ ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ *ምንጭ፡-የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 5፣የባለሥልጣን መ/ቤቱ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 2*
	3. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ተቋርጦ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ ፕሮጀክቶች ለዘላቂ የጥራት ችግር ከመጋለጣቸው በፊት ክትትል በማድረግ ወደ ውለታ የሚገቡበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊሰራ ይገባል ፡፡ *ምንጭ፡የባለሥልጣን መ/ቤቱ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 23-24*
	4. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው የተቋረጡፕሮጀክቶች የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና(Performance Guarantees) በውለታቸው መሰረት ገቢ የተደረገላቸው መሆኑን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ *ምንጭ፡ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 23*
	5. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በፌደራል መንግስት በጀት የሚገነቡ ውለታቸው ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎች ተመላሽ ስለመደረጋቸው ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡ የባለሥልጣን መ/ቤቱ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 25*

	6. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ እና ተገቢ የሆኑ ባለሙያዎች ስብጥር እንዲሟላ ሊያደርግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡-የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 3*
	7. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለተቋረጡ ፕሮጀክቶች ቁጥጥር እና ለሥራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ እና ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችን በማስጠናትና በጥናቱ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የባለሥልጣን መ/ቤቱ የ2014 በጀት አመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 3፣ደንብ ቁጥር 524/2015 አንቀጽ እና 5(19፣የ5 አመት እቅድ ገጽ 20)*
II. ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የሚያከናውኑ ድርጅቶች በሰራተኞች ደህንነትና ጤንነት ህጎች መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን መገምገም	8. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ ፣በባህላዊ ቅርሶች ፣በሠራተኞች እና በህብረተሰቡ ጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮችን ሊዘረጋና አፈፃፀማቸውንም ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ *ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር439/2011 እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ደንብ ቁጥር 524/2015፤የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 15*
	9. ባለሥልጣን መ/ቤቱ አካባቢን፣የሠራተኞችን እና የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት በተመለከተ የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅቶች የሚጠቀሟቸው የኮንስትራክሽን ውሎች ተመሳሳይ ስታንዳርድ የሚከተሉ መሆናቸውን ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር439/2011 እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ደንብ ቁጥር 524/2015፤የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 15*
	10.በኮንስትራክሽን ስራዎችና ግንባታዎች የአደጋ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊፈትሽ፣ ሪፖርት ሊያደርግ እና የህግ ተጠያቂነት እንዲኖር ሊከታተል ይገባል፡፡ *ምንጭ፡- ደንብ ቁጥር 524/2015 አንቀጽ እና 5(9) እና ደንብ ቁጥር 439/2011 አንቀጽ 5(14*
I. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ	11.በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማሩ የሥራ ተቋራጮችን ፈቃድ አሰጣጥ እና የፕሮጀክቶችን ቁጥጥርና ክትትል የሚመለከቱ

ተቋራጮችን ብቃት በማረጋገጥ የሚመዘግብበት እና ቁጥጥር የሚያደርግበት ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣	አዋጆች፣ደንቦች መመሪያዎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው በሚመለከተው አካል ጸድቀው ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ *ምንጭ:የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ገፅ 13-14*
	12.ለሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጮች (ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ፣ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ፣ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጥ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት (ማሽነሪ፣ አመታዊ ተርንኦቨርና የሰው ኃይል፣የመጫረቻ ዋጋ መጠን …) ያሟሉ መሆኑ የሚያረጋግጥበት የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ም ገፅ 32-33 እና 45-52*
	13.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሁሉም አይነት ሥራ ተቋራጭነት (ጠቅላላ፣ የህንፃ ፣ የመንገድ እና ልዩ ሥራ ተቋራጭ) ለሚሳተፉ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች በመመሪያው በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሙያ ፈቃድ ማረጋገጫ በመስጠት ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ም ገፅ 32*
	14.የሙያ ፈቃድ ማረጋገጫ የወሰዱ የሥራ ተቋራጮች ያስመዘገቧቸው (የሰው ኃይል፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች) ፈቃድ ለወሰዱበት ሥራ እየዋሉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል (በስራ ቦታው ላይ ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ የተመዘገቡት ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በስራ ላይ ስለመሆናቸው)በየአመቱ እቅድ በማዘጋጀት የሚጣራበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ:የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ምገፅ 16*
	15.ባለሥልጣን መ/ቤቱ የስራ ተቋራጮች ከመመሪያ ቁጥር 648/2013 በፊት የወሰዱትን የሙያ ማረጋገጫ በተሰጣቸው የመሸጋገሪያ ጊዜ በሚያሟሉት ደረጃ ዳግም የተመዘገቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኮንስትራክሽብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 648/2013 ዓ.ም*
	16.ከተሠጣቸው ደረጃ ውጭ የሚሰሩ እና ፈቃዳቸውን ለሌላ አካል

	አሳልፈው የሚሰጡ የሥራ ተቋራጮች እንዳይኖሩ ለመከላከል ሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡ ደንብ ቁጥር 524/2015 አንቀፅ 5 ቁጥር 12፣የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 648/2013 ዓ.ም ገፅ 16፣የኮንስትራክሽን ግንባታ ፕሮጀክቶች መቆጣጠሪያ እና ሪፖርት አዘገጃጀት ማኑዋል ገፅ 4*
	17.ከባለስልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮች በየሁለት ዓመቱ ፈቃድ ያሳደሱ መሆናቸውን ባለሥልጣኑ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ *ምንጭ:የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃትማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 648/2013 ዓ.ም ገፅ 12*
	18.የሥራ ተቋራጮች ፈቃድ ሲታደስ ለደረጃቸው የሚያስፈልገው (የሰው ኃይል፣ የስራ ላይ ስልጠና፣ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች) በሠነድና በአካል መኖራቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ *ምንጭ:የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ም አንቀፅ 24(1) ገፅ 12*
	19.በፌደራል እና በክልሎች፣በከተማ አስተዳደሮች ያለው በየደረጃው የሚከናወነው የስራ ተቋራጮች ፈቃድ አሰጣጥ፣የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሁም ተመሳሳይ ስታንዳርድ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኢትዮጵያኮንስትራክሽንባለሥልጣን፣ተግባርእና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 524/2015*
	20.ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚሰጣቸው የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አገልግሎት ስታንዳርድ እና የፕሮጀክቶችን ጥራት(quality) የሚቆጣጠርበት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅ ይገባል:: *ምንጭ: የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ገፅ 3፣legal gaps Analysis of construction supervision in Ethiopia August 2021 ላይ የተጠና ጥናት ገጽ 45*
	21.ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሥራ ተቋራጮች በሚሰጠው አገልግሎት ዙሪያ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያደርግበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ *ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የአምስት አመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ /2013-2017 /ዓ.ም ገፅ 36፣የ2014 በጀት አመት ዕቅድ ገፅ 13*

	22.የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚያወጡ ስራ ተቋራጮች አካል ጉዳተኛ/ሴት ከሆኑ በየደረጃው ከሚጠየቀው አመታዊ ተርን ኦቨር ብር መጠን በ15 መቶ ሊቀንስላቸው ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 648/2013 አንቀፅ 25(7)**
	23.በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግና የዘርፈብዙ ጉዳዮችን በማካተት በክህሎት ግንባታና አቅም ለመፍጠር የተለየ ፕሮጀክት ተቀርጾ ተግባራዊ የሚደረግበት የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ገጽ 106**
. የሥራ ተቋራጮችንና ፕሮጀክቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን መገምገም	24.ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሀገሪቷ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች እና የመንግስት ፕሮጀክቶችን እንደየምድባቸው መዝግቦ በመያዝ ሊቆጣጥር ይገባል፡፡ ***ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ሥራዎች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 439/2011እና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ደንብ ቁጥር 524/2015፣የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር648/2013 ዓ.ም ገፅ 20***
	25.ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም በፌዴራል መንግስት በጀት የሚገነቡ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የአፈጻጸም መረጃዎች (የተጠናቀቁ፣የዘገዩ የተቋረጡ….) መሆናቸውን አሰሪ መ/ቤቶች በየስድስት ወር ማሳወቃቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ ***ምንጭ፡የኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 648/2021 አንቀፅ 32(4)(6)***
	26.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ታዕማኒነት ያለው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ቋት ወይም ዳታ ቤዝ በማደራጀት መረጃ ሊይዝ ይገባል፡፡ ***ምንጭ፡የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ገጽ 89***
	27.ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፈቃድ የወሰዱ ሥራ ተቋራጮችን እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ከባለድርሻ አካላት (ከገንዘብ ሚ/ር፣ ከፕላንና ልማት ሚ/ር፣ከፕሮጀክት ባለቤቶች …ወዘተ) ጋር ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ***ምንጭ፡ የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን የአምስት አመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ /2013-2017 /ዓ.ም ገፅ 9***

አባሪ-3 በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ ተቋማት ዝርዝር

ተ.ቁ	የተቋማቱ ስም	የሚገኙበት ቦታ
1	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	ወላይታ ሶዶ
2	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	ሀዋሳ
3	ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ	ሀረማያ
4	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	ድረዳዋ
5	ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር	አዲስ አበባ
6	የፌዴራል መንግስት ህንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	አዲስ አበባ
7	ሲዳማ ክልል ኮንስትራክሽን ባለስልጣን	ሰዳማ
8	ኦሮሚያ ክልል ኮንስትራክሽን ባለስልጣን	አዲስ አበባ
9	ሐረሬ ክልል የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን	ሐራሪ
10	ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽ ቢሮ	ድሬዳዋ
11	ዛምራ ስራ ተቋራጭ	ዳዬ
12	ይርጋለም ስራ ተቋራጭ	አዲስ አበባ
13	ኦቪድ ስራ ተቋራጭ	አዲስ አበባ
14	አበራ ልሳኑ ስራ ተቋራጭ	ሀዋሳ
15	ዮሃንስ ኃይሌ ስራ ተቋራጭ	አዲስ አበባ
16	ኤስ ሀዊ ስራ ተቋራጭ	ሀረማያ
17	ሰንራይዝ ስራ ተቋራጭ	አዲስ አበባ

አባሪ-4፡ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያ ውለታቸው ባለመጠናቀቃቸው በመንግስት ላይ ያስከተሉትን ተጨማሪ ወጪ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	ፕሮጀክቱ ባለቤት	ፕሮጀክቱ ስም	ፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ		የፕሮጀክቱ የውል ዋጋ		
			በቀድሞ	በአሁኑ	በቀድሞ	በአሁኑ	ልዩነት
1	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	1. ዳውሮ ታርጫ የአስተዳደር ፣የተማሪዎች ክሊኒክ እና የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃ	ዮሐንስ ኃይሌ	ብራይትና ሆማ (39,955,763.44) ሶሊያናተቋራጭ (239,819,131.03) አበራ ልሳኑ (311,828,561.22)	136,844,513.96ETB	591,603,455.69ETB	454,758,941.73ETB
		2. የተማረዎች መማሪያ ክፍሎች በዋና ግቢ	ዮሐንስ ኃይሌ	ጥለሁን አበበ	113,940,992.37ETB	245,964,598.64ETB	132,023,606.27ETB
		3. የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃ በዋና ግቢ	እቴቴ ስራ ተቋራጭ	ዮሐንስ ኃይሌ (259,968,032.10) አበራ ልሳኑ (126,708,100.63)	151178572.59 ETB	386,676,132.73ETB	235,497,560.14ETB
2	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	4. ዘመናዊ ገራጅ ግንባታ በዋና ግቢ	ቢሃ	ኤስ ሀዊ	94,505,184.73 ETB	504,450,542.75 ETB	409,945,358.02 ETB
		5. ኤሌክትሪክ ኃይል ስቴሽን	ኤልቴል	ሆኮ	2,533,410.00USD+ 7,857,672 ETB	554,261,394.56 ETB	501,352,852.553 ETB

		ግንባታ			=(52,908,542.07 ETB)		
3	የፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	6. በቀድሞ የኮሚንከሽን ጉዳይ በአሁኑ የንግድና ኢንዱያስትሪ ሚኒስቴር ቢሮ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኮርፖረሽን	1,207,195,702.89 ETB	1,243,738,399.47 ETB	36,542,696.58 ETB
		7. የሲቪል አቬንሽን ዋና መ/ቤት ግንባታ	ቢሃ	ሳንታ ማሪያ	292,566,405.68 ETB	2,497,172,128.60 ETB	2,204,605,722.92 ETB
		8. የብሔራዊ ቲአትር ግንባታ	አፍሮጺዮን	ኦቪድ	1,497,202,550.29 ETB	2,727,110,612.45 ETB	1,229,908,062.16 ETB
		9. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	አፍሮጺዮን	ይርጋለም	1,135,490,490.91 ETB	4,123,545,247.62 ETB	2,988,054,756.71 ETB
4	ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር	10. አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ	ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ	አለማየሁ ከተማ	1,167,676,338.95 ETB	5,106,525,941.61 ETB	3,938,849,602.66 ETB
		11. አቦምሳ - አሰኮ - ዲቡወንዝ	ተክለብርሃን አምባዬ	ሀቨሪም ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ከአለማየሁ ከተማ	991,721,997.83 ETB	2,260,899,043.09 ETB	1,269,177,045.26 ETB

				ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ			
		12. ሮቤ-ሴሩ	ተክለብርሃን አምባዬ	ዩኒፕሬሳ እስፓ	993,181,495.38 ETB	2,291,343,381.66 ETB	1,298,161,886.28 ETB
		13. ወራቤ-ቦጆበር	ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ	አማራ መንገድ ሥራዎች	795,000,000 ETB	2,777,252,940.36 ETB	1,982,252,940.36 ETB
		ጠቅላላ ድምር			8,629,412,788	25,310,543,819	16,681,131,031.64

አባሪ-5፡

ውለታቸው ተቋርጦ በድጋሜ ወደ ግንባታ የገቡ ፕሮጀክቶች የተጀመሩበት ጊዜ፣መጠናቀቅ የነበረባቸው ጊዜ፣የተቋረጡበት ጊዜ እና የተቋረጡበትን ምክንያት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	ፕሮጀክቱ ባለቤት	ፕሮጀክቱ ስም	ፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ	ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ጊዜ	ፕሮጀክቱ መጠናቀቅ የነበረበት ጊዜ	ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ጊዜ	ፕሮጀክቱ የተቋረጠበት ምክንያት
1	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	1.ዳውሮ ታርጫ የአስተዳደር ፣የተማሪዎች ክሊኒክ እና የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃ	ዮሐንስ ኃይሌ	26/03/2008 E.c	17/02/2009 E.c	04/10/11 E.c	ከፍተኛ የስራ ለውጥ /high variation/
		2.የተማረዎች መማሪያ ክፍሎች በዋና ግቢ	ዮሐንስ ኃይሌ	26/03/2008 E.c	17/12/2009 E.c	04/10/11 E.c	ከፍተኛ የስራ ለውጥ /high variation/
		3.የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃ በዋና ግቢ	እቴቴ ስራ ተቋራጭ	26/03/2008 E.c	17/12/2009 E.c	04/10/11 E.c	ከፍተኛ የስራ ለውጥ /high variation
2	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	4.ዘመናዊ ገራጅ ግንባታ በዋና ግቢ	ቢሃ	18/7/2007 E.c	18/11/2008 E.c E.c	18/4/2011 E.c	የስራ ተቋራጩ አቅም ማነስ ምክንያት በተሰጠው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉ
		5.ኤሌክትሪክ ኃይል ስተሽን ግንባታ	ኤልቴል	15/10/2004 E.c	5/11/2006 E.c		በውጭ ምንዛሬ እጥረት
3	የፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	6.በቀድሞ የኮሚንከሽን ጉዳይ በአሁኑ የንግድና ኢንዱያስትሪ ሚኒስቴር ቢሮ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	12/5/2008 E.c	11/2/2011 E.c	20/3/2012 E.c	የስራ ተቋራጩ አቅም ማነስ ምክንያት በተሰጠው ጊዜ ማጠናቀቅ ባለመቻሉ

		7.የሲቪል አቬንሽን ዋና መ/ቤት ግንባታ	ቢሃ	20/4/2010 E.c	23/5/2012 E.c	22/6/2012 E.c	ለስራ ተቋራጩ ተጨማሪ ጊዜ ተሰቶ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ዝቅተኛ(32.77%) በመሆኑ ምክንያት
		8.የብሔራዊ ቲአትር ግንባታ	አፍሮጺዮን	3/6/2011 E.c	2/10/2013 E.c	26/112011 E.c	ስራ ተቋራጩ በእቅዱ መሰረት የፕሮጀክቱ ግንባታ 50% ማድረስ ሲገባው አፈጻጸሙ 5% ብቻ በመሆኑ
		9.የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	አፍሮጺዮን	1/12/2010 E.c	28/2/2013 E.c	26/5/2013 E.c	ስራ ተቋራጩ በእቅዱ መሰረት የፕሮጀክቱ ግንባታ 97.55% ማድረስ ስገባ አፈጻጸሙ 14.73% ብቻ በመሆኑ
4	ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር	10. አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ	ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ	17/09/2009 E.c	7/05/2014 E.c	26/01/2022 E.c	ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈለጉ ቁሳቁሶች ማቅረብ በለመቻሉ እና በፕሮጀክቱ ሳይት ላይ ምንም አይነት የስራ እንቅስቃሰ በለመኖሩ
		11. አቦምሳ - አሰኮ - ዲቡወንዝ	ተክለብርሃን አምባዬ	25/12/2009 E.c	08/02/2014 E.c	1/10/2012 E.c	ስራ ተቋራጩ በውሉ መሰረት ስራውን ማከናወን በለመቻሉ
		12. ሮቤ-ሴሩ	ተክለብርሃን አምባዬ	03/10/ 2010 E.c	16/05/2014 E.c	26/6/2020 E.c	ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና ማሽነሪዎች በውሉ መሰረት ባለማቅረቡና ባለመጠቀሙ
		13. ወራቤ-ቦጆበር	የማነ ግርማይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ	26/05/2009 E.c	04/06/2015 E.c	10/5/2015 E.c	ስራ ስራ ተቋራጩ ለፕሮጀክቱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እና ማሽነሪዎች በውሉ መሰረት ባለማቅረቡና ባለመጠቀሙ

አባሪ-6፡

ፕሮጀክቶች ሲቋረጡ ሳይት ላይ የነበሩ ንብረቶችን ሁኔታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ባለቤት	የፕሮጀክቱ ስም	የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ	ፕሮጀክቱ ሲቋረጥ ሳይቱ ላይ የነበሩ ንብረቶች ያሉበት ሁኔታ		መግለጫ
				የተመዘገቡ	ያልተመዘገቡ	
1	ወላታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ	1.ዳውሮታርጫ ካምፓስ የአጥር ግንባታ	አዱኛ ለማ		✓	
		2. ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የመምህራን መዝናኛና ሽንት ቤትና ሻወር ግንባታ	ማርቆስ መንገሻ		✓	
		3. በዳውሮ ታርጫ የመማሪያ ክፍሎች	ብርሃን ጠቢያው		✓	
		4. በዋና ጊቢ የአመራሮች መኖሪያ	ጌታቸው አባይ		✓	
		5. የዳውሮ ታርጫ የአስተዳደር ህንጻ፣የተማሪዎች ክሊንክ እና የተማሪዎች ማደሪያ	ዮሐንስ ኃይሌ		✓	
		6.በዋና ጊቢ የመማሪያ ክፍሎች	ዮሐንስ ኃይሌ		✓	
		7.በዋና ጊቢ የተማሪዎች ማደሪያ	እቴቴ		✓	
2	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	8.የጤና ካምፓስ የተማሪዎች መማሪያ፣ ማደሪያ፣ካፍተሪያ እና የሰራተኛ መኖሪያ	ፍልንትስቶን	✓		
		9.በዳዬ ካምፓስ የተማሪዎች ማደሪያ፣ የመጋዘን፣የሰራተኛ መኖሪያ እና የካፍተሪያ	ተክለብርሃን አምባዬ	✓		
		10. የቴክኖሎጅካምፓስ የቤተ መፅሐፍ፣ የተማሪዎች መመገቢያዎች እና የመጋዘን ግንባታ	መስኮን		✓	

		11. የወንዶገነት ካምፓስ የአጥር ግንባታ	ስንታዬሁ ወ/ጊዮርግስ	-	-	ስራው ሳይ ጀመሩ ውላቸ የተቋረጠ
3	ሐረማያ ዩኒቨርስቲ	12. የዘመናዊ ገራጅ፣	ቢ.ሃ	✓		
		13. የኤሌክትሪክ ስተሽን ግንባታ	ኤልቴል	✓		
		14. ኬሚካል ስቶር	ሞውልድ ኢስማኤል		✓	
		15. ጉርሱም ምርምር ማዕከል	በቀሌ ቡርሳ	✓		
		16. የህዎት ፋና ሪፈራል ሆስፕታል	አፍሮ ጽዮን	✓		
		17. ቶንይ እርሻ ምርምር ማዕከል አጥር ግንባታ	አፍሪካዊት	✓		
		18. የሀራራ ካምፓስ አጥር ግንባታ	አዊሀክም	-	-	ስራው ሳይጀመር ውላቸ የተቋረጠ
		19. የፅኖ ህማማን ሆስፕታል	ያሬድ	✓		
4	ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ	20. የአጥርእና ምድረግቢ	ዳዊት ሀ/ማርያም		✓	
		21. የተማርዎች መኖሪያ ጥገና ሎት 1	የት ኮንስትራክሽን ፣ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን እቃዎች አቅራቢ		✓	
		22. የተማርዎች መኖሪያ ጥገና ሎት 2	የት ኮንስትራክሽን ፣ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን እቃዎች አቅራቢ		✓	
		23. የአስተዳደር ህንጻ	3ኤም ኢንጅነርንግ	✓		
		24. የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና መሰረተ ልማት ግንባታ	አፍሮጽዮን	✓		

5	የፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	25. በቀድሞ የኮሚኒኬሽን ጉዳይ በአሁኑ የንግድና ኢንዲያስትሪ ሚኒስቴር ቢሮ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	✓		
		26. ሲቪል አቬንሽን ዋና መ/ቤት ግንባታ	ቢሃ	✓		
		27. የብሔራዊ ቲአትር ግንባታ	አፍሮጺዮን	✓		
		28. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢሮና ዲፕሎማቶች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	አፍሮጺዮን	✓		
		29. የፌዴራል ዳኞች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	✓		
		30. የከፍተኛ ባለስልጣናት መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	✓		
		31. የኢንፎሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት ግንባታ	መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይስ	✓		
6	የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር	32. ሎት 1፡ ፍሰሃ ገነት - ኬሌ - ነደሌ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት	ሻንዶንግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ (በአሁኑ ሥሙ ቻይና ናሽናል ኬሚካል ኮምዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ግሩፕ)	✓	-	
		33. ኢትዮጵያ ኢንተግሬትድ ትራንስፖርት ፕሮግራም ፌዝ 1፡ ጅማ — ጭዳ እና ሶዶ — ሳውላ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት; ሎት 3፡ ድንኬ — ሳውላ ሴክሽን	ቤጅንግ አርባን ኮንስትራክሽን ግሩፕ ኮ ሊትድ	✓		
		34. ጩሉሴ-ሶያማ	ቻይና ሬልዌይ 14ኛ ቢሮ ግሩፕ ኮ ሊትድ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ	✓		

		35. ተርጫ -ጭዳ	ኢንቨስሮይፒሮከት ኤለአልሲ	✓		
		36. አጣጥ ማዞሪያ - ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ	ሻንዶግ ሃይ ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ ካምፓኒ ሊሚትድ	✓		
		37. ጋሴራ-ጊኒር	አፍሮፅዮ ንኮንስትራክሽን	✓		
		38. አቦምሳ-አሰኮ - ዲቡወንዝ	ተክለብርሃን አምባዬ	✓		
		39. ዲቡወንዝ -በደይ - ጨለለቃ	ተክለብርሃን አምባዬ	✓		
		40. ሮቤ-ሴሩ	ተክለብርሃን አምባዬ	✓		
			ዩኒፕሬሳ እስፓ	✓		
		41. ወራቤ-ቦጀበር	የማነ ግርማይ	✓		
			ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ	✓		

አባሪ-7፡-

ተመላሽ ያልተደረገ ቅድመ ክፍያ እና የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናን መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ባለቤት	የፕሮጀክቱ ስም	የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ	ለፕሮጀክቱ የተከፈለ ቅድመ ክፍያ መጠን (ብር)	ተመላሽ የተደረገ ቅድመ ክፍያ መጠን (ብር)	ተመላሽ ያልተደረገ ቅድመ ክፍያ መጠን (ብር)	የፕሮጀክቱ መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መጠን (ብር)	የፕሮጀክቱ ውል ሲቋረጥ ገቢ የተደረገ መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መጠን (ብር)	የፕሮጀክቱ ውል ሲቋረጥ ገቢ ያልተደረገ መልካም ስራ አፈፃፀም ዋስትና መጠን (ብር)	መግለጫ
1	ወላታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ	1.ዳውሮታርጫ ካምፓስ የአጥር ግንባታ	አዱኛ ለማ	773,191.22	-	773,191.22	257,730.41	-	257,730.41	
		2. ዳውሮ ታርጫ ካምፓስ የመምህራን መዝናኛና ሽንት ቤትና ሻወር ግንባታ	ማርቆስ መንገሻ	2,044,892.64	284,409.81	1,760,482.83	681,630.88	-	681,630.88	
		3. በዳውሮ ታርጫ የመማሪያ ክፍሎች	ብርሃን ጦቢያው	24,038,059.01	18,942,714.84	5,095,344.17	8,012,686.33	-	8,012,686.33	
		4 በዋና ጊቢ የአመራሮች መኖሪያ	ጌታቸው አባይ	8,317,959.58	826,662.20	7,491,297.38	4,158,979.79	-	4,158,979.79	

		IV.የጻውሮ ታርጫ የአሰተዳደር ህንጻ፣የተማሪዎች ክሊንክ እና የተማሪዎች ማደሪያ	ዮሐንስ ኃይሌ	------------	----------	-----------	13,684,451.39	-	13,684,451.39	
		V. በዋና ጊቢ የመማሪያ ክፍሎች	ዮሐንስ ኃይሌ	----------	----------	-----------	11,394,099.23	-	11,394,099.23	
		VI. በዋና ጊቢ የተማሪዎች ማደሪያ	እቴቴ	----------	----------	----------	15,117,847.26	-	15,117,847.26	
አጠቃላይ				<u>105,359,795.97</u>	<u>90,239,480.37</u>	<u>15,120,315.60</u>	<u>53,307,425.29</u>	0	<u>53,307,425.29</u>	
2	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	VII. የጤና ካምፓስ የተማሪዎች መማሪያ፣ ማደሪያ፣ካፍተሪያ እና የሰራተኛ መኖሪያ	ፍልንትስቶን	----------	----------	----------	17,028,423.00	-	17,028,423.00	
		VIII. በዳዬ ካምፓስ የተማሪዎች ማደሪያ፣ የመጋዘን፣የሰራተኛ መኖሪያ እና የካፍተሪያ	ተክለብርሃን አምባዬ	----------	----------	----------	65,021,595.85	-	65,021,595.85	
		IX. የቴክኖሎጅካምፓስ	መስኮን	----------	----------	0	29,363,693.79	-	29,363,693.79	

		የቤት መፅሐፍ፣ የተማሪዎችመመገቢያዎች እና የመጋዘን ግንባታ								
		የወንዶገነት ካምፓስ የአጥር ግንባታ	ስንታዬሁ ወ/ጊዮርግስ	1,133,720.56	130,355.55	1,003,365.01	566,860.28	-	566,860.28	
				<u>296,371,046.87</u>	<u>295,367,681.86</u>	<u>1,003,365.01</u>	<u>147,638,474.98</u>	0	<u>111,980,572.92</u>	
3	ሐረማያ ዩኒቨርስቲ	የዘመናዊ ገራጅ፣	ቢሃ	18,901,036.95	9,542,763.81	9,358,273.14	9,450,518.47	-	9,450,518.47	
		. የኤሌክትሪክ ስተሽን ግንባታ	ኤልቴል	----------	----------	----------	6,750,704.14	-	6,750,704.14	
		I. ኬሚካል ስቶር	ሞውልድ ኢስማኤል	----------	----------	----------	715,207.53	-	715,207.53	
		/. ጉርሱም ምርምር ማዕከል	በቀሌ ቡርሳ	----------	----------	----------	1,502,564.74	-	1,502,564.74	
		. የህዎት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል	አፍሮ ጽዮን	275,605,786.39	243,100,385.26	32,505,401.13	127,706,727.07	-	127,706,727.07	
		I. ቶንይ እርሻ ምርምር ማዕከል አጥር ግንባታ	አፍሪካዊት	----------	----------	----------	5,019,961.47	-	5,019,961.47	
		II. የሀራሩ ካምፓስ አጥር ግንባታ	አዊሀክም	4,910,064.48	2,712,295.85	2,197,768.63	1,899,672.66	-	1,899,672.66	
		III. የፅኖ ህማማን	ያሬድ	----------	----------	----------	2,322,054.99	-	2,322,054.99	

		ሆስፕታል							
				320,375,422.69	**261,429,969.97**	**44,061,442.90**	**155,367,411.07**	0	**155,367,411.07**
4	ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ	X. የአጥርእና ምድረግቢ	ዳዊት ሀ/ማርያም	10,929,156.68	5,631,609.65	5,297,547.03	3,643,052.23	-	3,643,052.23
		. የተማርዎች መኖሪያ ጥገና ሎት 1	የት ኮንስትራክሽን ፣ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን እቃዎች አቅራቢ	----------	----------	----------	883,037.51	-	883,037.51
		I. የተማርዎች መኖሪያ ጥገና ሎት 2	የት ኮንስትራክሽን ፣ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን እቃዎች አቅራቢ	4,298,166.11	1,742,872	2,555,294.29	1,426,373.84	-	1,426,373.84
		II. የአስተዳደር ህንጻ	3ኤም ኢንጅነርንግ	51,133,402.05	50,628,183.89	505,218.16	17,044,467.35	-	17,044,467.35
		III. የተማሪዎች መማሪያ ክፍል እና	አፍሮጽዮን	69,143,360.36	17,154,520.15	51,988,840.21	34,571,680.18	-	34,571,680.18

		መሰረተ ልማት ግንባታ								
				138,153,197.74	**77,806,298.05**	**60,346,899.69**	**57,568,611.11**	0	**57,568,611.11**	
5	የፌዴራል መንግስት ህንፃዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት	IV. በቀድሞ የኮሚኒኬሽን ጉዳይ በአሁኑ የንግድና ኢንዱያስትሪ ሚኒስቴር ቢሮ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	241,439,140.6	71,174,300.29	170,264,840.31	120,719,570.29	-	120,719,570.29	
		V. ሲቪል አቬንሽን ዋና መ/ቤት ግንባታ	ቢሃ	58,513,281.14	39,445,532.25	19,067,748.89	43,884,960.85	-	43,884,960.85	
		XXVI. የብሔራዊ ቲአትር ግንባታ	አፍሮጺዮን	224,537,330.43	8,883,289.45	215,654,040.98	149,720,255.03	-	149,720,255.03	
		XXVII. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቢሮና ዲፕሎማቶች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	አፍሮጺዮን	227,098,098.18	34,264,846.85	192,833,251.33	113,549,049.09	-	113,549,049.09	
		XXVIII. የፌዴራል ዳኞች መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	ቴክለ ብርሃን አምባዬ	----------	----------	----------	91,827,853.01	-	91,827,853.01	
		XXIX. የከፍተኛ	ቴክለ ብርሃን	----------	----------	----------	15,407,950.75	-	15,407,950.75	

		ባለስልጣናት መኖሪያ ህንጻ ግንባታ	አምባዬ							
		XXX. የኢንፎሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ዋና መ/ቤት ግንባታ	መከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይስ	----------	----------	--------------	203,272,802.83	-	203,272,802.83	
				1,507,061,973.41	**909,242,091.90**	**597,819,881.51**	**738,382,441.85**	-	**738,382,441.85**	
6	የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳዳር	XXXI. ሎት 1፡ ፍሰሃ ገነት - ኬሌ - ነደሌ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት	ሻንዶንግ ሃይዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ (በአሁኑ ሥሙ ቻይና ናሽናል ኬሚካል ኮምዩኒኬሽን ኮንስትራክሽን ግሩፕ)	325,404,036.076	-	325,404,036.076	161,200,686.68	-	161,200,686.68	

		XXXII. ኢትዮጵያ ኢንተግሬትድ ትራንስፖርት ፕሮግራም ፌዝ 1፡ ጅማ — ጭዳ እና ሶዶ — ሳውላ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት; ሎት 3፡ ድንኬ — ሳውላ ሴክሽን	ቤጅንግ አርባን ኮንስትራክሽን ግሩፕ ኮሊትድ	189,151,930.637	84,831,240.18	104,320,690.45	103,595,581.1769	-	103,595,581.1769	
		XXXIII. ጪለሴ-ሶያማ	ቻይና ሬልዌይ 14ኛ ቢሮ ግሩፕ ኮሊትድ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ	227,386,499.056	-	227,386,499.056	206,385,758.68	-	206,385,758.68	
		XXXIV. ተርጫ -ጭዳ	ኢንቨስሮይፒሮከት ኤለአልሲ	------------------	-------------	------	------		------	
		XXXV. አጣጥ ማዞሪያ	ሻንዶግ ሃይ	233,059,918.9	53,007,972.93	180,051,945.97	117,823,523.0	-	117,823,523.099	

		- ጉንችሬ - ኮሴ - ጌጃ - ሌራ	ዌይ ኢንጂነሪንግ ኮንስትራክሽን ግሩፕ ካምፓኒ ሊሚትድ				99			
		XXXVI. ጋሴራ-ጊኒር	አፍሮፅዮንኮንስትራክሽን	168,320,403.8	-	168,320,403.8	84,160,201.92	-	84,160,201.92	
		XXXVII. አቦምሳ-አሰኮ - ዲቡወንዝ	ተክለብርሃን አምባዬ	176,823,088.2	-	176,823,088.2	99,172,199.78	-	99,172,199.78	
		XXXVIII. ዲቡወ ንዝ -በደይ - ጨለለቃ	ተክለብርሃን አምባዬ	129,109,555.18	-	129,109,555.18	72,562,142.82	-	72,562,142.82	
		XXXIX. ሮቤ-ሴሩ	ተክለብርሃን አምባዬ	89,609,174.02	55,524,563.57	34,084,610.45	99,318,149.538	-	99,318,149.538	
			ዩኒፕሬሳ እስፓ	207,719,848.21	-	207,719,848.21	232,294,839.55	-	232,294,839.55	
		XL. ወራቤ-ቦጀበር	የማነ ግርማይ	91,689,130	-	91,689,130	45,844,565	-	45,844,565	
			ማርካን ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ	159,000,000	54,466,384.96	104,533,615.07	79,500,000	-	79,500,000	

				1,997,273,584.08	247,830,161.52	*1,749,443,422.46*	1,301,857,648.24	0	1,301,857,648.24	
				3,220,090,230.36		2,467,795,327.17			2,411,544,476.35	